
# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል



**ይህንን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ ተጠቀምበት/ሚበት**




ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ሽ ንብረት ነው። ጉዳት እንዳታደርስበት/ሺበት ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቅ/ጠብቂ።

ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ መከተል ያለበትን መመሪያዎች ተጠቀም/ሚ

1. መጽሐፉን በጋዜጣ፣ በፕሊስቲክ ወይም በተገኘው ወረቀት ሽፍን/ኚ ፡፡
2. መጽሐፉን ሁሌጊዜ ደረቅ እና ንፁህ በሆነ ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡
3. መጽሐፉን ሁሌጊዜ በንፁህ እጅ ያዝ/ዢ፡፡
4. መጽሐፉን ላይ ምንም አይነት ፅሁፍ አትፃፍ/ፊ፡፡
5. የምትፈልገውን/ጊውን ቦታ በመክፈት ካርድ ወይም ብጣሽ ወረቀት እንደ ምልክት በማስቀመጥ ተጠቀም/ሚ ፡፡
6. አንድም ገፅ ወይም አንድም ስዕል ከውስጡ ለመቅደድ አትሞክር/ሪ፡፡
7. የተቀደደ ገፅ ካለ በማስትሽ ወይም በፕሊስተር አያይዝ/ዢ፡፡
8. በመንገድ ላይም መጽሐፍ በማይጎዳ ሁኔታ ያዝ/ዢ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታውስ/ሺ በጥንቃቄ ይሁን፡፡
10. በአዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀም/ሚ፣ መጽሐፉን በጀርባ በማስቀመጥ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ገልብጥ/ጪ፡፡ ቀስ ብለህ/ሽ የመጽሐፉን መሃል በእጅህ/ሽ ጫን በል/ይ፡፡ ይህም ዘዴ የመጽሐፉን ሽፋን እንዳይጎዳ ይረዳል፡፡

# ሒሳብ 3ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ

**አዘጋጆች**

ቦርቶላ ተሾመ

ስመኝ ተሰማ

**ኤድተሮች**

ተስፋዬ ጉደታ

ታደሰ ረጋሣ

**ተርጓሚዎች**

እሸቱ ቱፋ

ተክለማርያም ጉተማ

ጋሻሁን ዋሚ

**ገምጋሚዎች**

ጥላሁን አለሙ

አየለ በቀለ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቂ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምዕራፍ 1፡ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው ........................1
1.1. እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ክለሳ ................................................ 1
1.2. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማስላት............................................... 5
1.3. እስከ 10,000 ያሉ የ100 እና 1000 ብዜቶች............................................9
1.4. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች............................................... 11
1.5. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው ማስቀመጥ..................13
ምዕራፍ 2፡ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ.................. 17
2.1. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መ□መር........................................... 17
2.2. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ.......................................... 22
2.3. ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዘ የቃላት ፕሮብሌሞች...................... 26
ምዕራፍ 3፡ እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት...................................... 29
3.1. የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ዲጂት ቁጥር ማባዛት.................................. 29
3.2. ብዜታቸው 1000 በታች የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ዲጂት ማባዛት......... 32
3.3. ከማባዛት ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች ........................................ 37
ምዕራፍ 4፡ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል........................................ 39
4.1. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የማካፈል ክለሳ...................................... 39
4.2. እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለቀሪ ለ2 ማካፈል.................................40
4.3. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ2 እና ለ10 ማካፈል .............................. 42
4.4. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ1 ማካፈል........................................... 45
4.5. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ3፣ ለ4፣ ለ5፣ ለ6፣ ለ7፣ ለ8 እና ለ9 ማካፈል ........................................................................... 45
4.6. ከቃላት ፕሮብሌሞች ጋር የተገናኙ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል .................................................................................... 53
ምዕራፍ 5፡ የክፍልፋዮች መግቢያ............................................................. 55
5.1. ስለ ግማሽ ፣ ሲሶ እና ሩብ የታወቁ ምሳሌዎችን በቁጥሮች መግለፅ .......... 55

5.2. ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች ........................................ 56

5.3. የሙሉ ቁጥሮች፣ ግማሾች እና ሩቦች ................................................. 59

5.4. አቻ ክፍልፋዮችን ማሳየት.......................................................................60

ምዕራፍ 6፡ ፓተርኖች ....................................................................................... 63

6.1. እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖችን መለየት ............................................. 63

6.2. እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖችን ማስቀጠል........................................... 65

6.3. በሚደጋገሙና እየጨመሩ በሚሄዱ ፓተርኖች ዉስጥ ርቀዉ የሚገኙ አባሎችን መገመት.......................................................................... 67

6.4. ከፓተርን ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች ................................................... 68

ምዕራፍ 7፡ የዳታ አያያዝ ............................................................................... 71

7.1. የስዕል ግራፎች ..........................................................................................71

7.2 የግራፍ ምስሎችን ማንበብ እና መግለፅ .............................................. 75

ምዕራፍ 8፡ የጂኦሜትር ምስሎች ....................................................................... 78

8.1. ምስሎችን በጎንዮሽ ዙር፤ በማንቀሳቀስ እና ነቁጦችን በማዞር የሚገኙ ውጤቶችን መገንዘብ ...................................................................... 78

8.2. ሲሜትሪክ እና ሲሜትሪክ ያልሆኑ ቅርፆች..............................................82

8.3. የተለያዩ የጂኦሜትሪ ምስሎች ስያሜ እና ባላቸው የጎን ብዛት መለየት.............84

8.4. የጂኦሜትረ ምስሎችን ባህሪያት በመገንዘብ መጥቀስ .............................. 88

ምዕራፍ 9፡ የርዝመት መጠነ ቁስ እና ይዘት መስፈሪያ ዩኒቶች ............................ 91

9.1. ርዝመትን ፣ በሚሊ ሜትር፣ ሴንቲ ሜትር ፣ በሜትር እና በኪሎ ሜትር መስፈር .................................................................................................... 91

9.2. ተመሳሳይ የርዝመት ዩኒቶች ያላቸውን መስፈሪያዎች መደመር እና መቀነስ................................................................................................... 94

9.3. መጠነ ቁስን በሚሊ ግራም በግራም፤ በኪሎ ግራም እና በኩንታል መስፈር........................................................................................................ 96


9.4. ተመሳሳይ የመጠነ-ቁስ መስፈሪያ ዩኒት ያላቸውን መደመር እና መቀነስ.......98

9.5. የይዘት መስፈሪያ ዩኒቶች ሚሊ ሊትር እና ሊትር ...................................99

9.6. ተመሳሳይ የይዘት መስፈሪያ ዩኒቶች ያላቸውን መደመር እና መቀነስ .......101

9.7. ከርዝመት፣መጠነ ቁስ እና ይዘት ጋር ተዛማችነት ያላቸው የቃላት ፕሮብሌሞች ........................................................................102
ምዕራፍ10 ፡ የኢትዮጵያ የገንዘብ ምንዛሬ ........................................................103
10.1. የምንዛሬ ዩኒቶችን መቀየር........................................................103
10.2 ከኢትዮጵያ የገንዘብ ምንዛሬ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት ........................................................................107
ምዕራፍ 11፡ የኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ........................................................110
11.1. ሰዓትን ማንበብ ........................................................................110
11.2. ሰዓት እና ደቂቃ ........................................................................112
11.3. ቀናት ፣ ሳምንታት ፣ ወራት እና አመታት ........................................ 114
11.4. የኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ........................................................ 115
11.5. ከኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ጋር ተዛምዶ ያላቸው የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት........................................................................ 116

# ምዕራፍ 1





# እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እና ቅደም ተከተላቸው





## 1.1 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ክለሳ

### ትግበራ 1.1

ከዚህ በታች የተሰጡትን የክዩብ ሞዴሎች በመቁጠር መቶዎች ፣ አስሮች እና አንዶችን ለይ/ዪ::




## ምሳሌ 1

| ስንት መቶዎች፣ አስሮች እና አንዶች አለው? | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | 2. | | |
|  |  |  |  |  |  |
| 4 መቶዎች | 4 አስሮች | 7 አንዶች | 3 መቶዎች | 5 አስሮች | 6 አንዶች |
| 400 | 40 | 7 | 300 | 50 | 6 |

## ምሳሌ 2

በአባከስ የተመለከቱት ቁጥሮች ስንት ናቸው?

ሀ.




| የመቶ ቤት ዋጋ | የአስር ቤት ዋጋ | የአንድ ቤት ዋጋ |
|---|---|---|

4 መቶዎች, 3 አስሮች እና 4 አንዶችን እናገኛለን

ይኸውም 400 + 30 + 4 = 434

ለ.



| የመቶ ቤት ዋጋ | የአስር ቤት ዋጋ | የአንድ ቤት ዋጋ |
|---|---|---|

3 መቶዎች, አስሮች 4

3 አንዶችን እናገኛለን

ይኸውም 300 + 40 + 3 = 343

## ምሳሌ 3

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ሰባት መቶ አስራ ስምንት

700 + 10 + 8 = 718

ለ. አምስት መቶ ዘጠኝ

500 + 9 = 509

ሐ. ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስምንት

900 + 60 + 8 = 968

መ. ስድስት መቶ ዘጠና አራት

600 + 90 + 4 = 694

2. የተሰጡትን ቁጥሮች በፊደል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 752 ለ. 904



## መፍትሂ

ሀ. 752፡ ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት


ለ. 904፡ ዘጠኝ መቶ አራት

## መልመጃ 1.1

1. ከታች የተሰጡት ክዩብ ሞዴሎችን የሚተካ ቁጥር በመምረጥ አክብ/ቢ፡፡


| ሀ. | | | ለ. | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  | | |  | | |
| 532 | 352 | 325 | 511 | 115 | 151 |

ሐ.




443 434 344

መ.




523 235 532

ሠ.



534 354 453


ረ.



112 212 122

2. በአባከስ ምስል የተመለከቱትን ቁጥሮች ትክክል የሆነው ላይ አክብብ፡፡


ሀ.



የመቶ ቤት የአስር ቤት የአንድ ቤት



745 547 457

ለ.



የመቶ ቤት የአስር ቤት የአንድ ቤት

465 546 645

| ሐ.  | የመቶ ቤት የአስር ቤት የአንድ ቤት | | መ.  | የመቶ ቤት የአስር ቤት የአንድ ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 587 | 857 | 758 | 516 | 506 | 56 |

3. በፊደል የተሰጡትን በአኃዝ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስድስት    ለ. ሶስት መቶ ሰባ ስድስት

ሐ. ሶስት መቶ ሰባ    መ. ስምንት መቶ አራት

4. በአኃዝ የተሰጡትን በፊደል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 649    ለ. 799    ሐ. 859    መ. 812

5. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 527    ለ. 578    ሐ. 643

መ. 916    ሠ. 999    ረ. 456

# 1.2 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማስላት

## ሀ. ባለ ሁለት ዲጂት ቁጥሮችን መደመር

### ምሳሌ 4

ሀ. 52 እና 45 ድምር/ሪ::    ለ. 57 እና 35 ድምር/ሪ::

| መጀመሪያ አንዶችን ደምር/ሪ | በመቀጠል አስሮችን ደምር/ሪ | መጀመሪያ አንዶችን ደምር/ሪ | በመቀጠል አስሮችን ደምር/ሪ |
|---|---|---|---|
| 52<br>+ 45<br>7<br>2+5=7 | 52<br>+ 45<br>97<br>5+4=9<br><br>52 + 45 = 97 | 1<br>57<br>+ 35<br>2<br>7+5=12<br>12 = 1 የአስር ቤት<br>እና 2 የአንድ ቤት | 1<br>57<br>+ 35<br>92<br>1+5+3 = 9<br><br>57 + 35 = 92 |

## መልመጃ1.2

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምር/ሪ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. 47 + 31 | ለ. 66 + 19 | ሐ. 39 + 36 | መ. 80 + 68 | ሠ. 53 + 78 |
| ረ. 59 + 40 | ሰ. 75 + 18 | ሸ. 49 + 65 | ቀ. 44 + 46 | በ. 88 + 39 |

2. በአንድ ት/ቤት ውስጥ 25 ወንድ መምህራን እና 17 ሴት መምህራን አሉ፡፡
3. አብደታ ባለው 82 ብር ላይ አባቱ 60 ብር ቢጨምርለት ስንት ብር ይኖረዋል?

## ለ. ባለሁለት ዲጂት ቁጥሮችን መቀነስ

### ምሳሌ 5

አቶ ቀጄላ 68 የቡና ችግኞች ተከሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ 12 ቢደርቁ ስንት የቡና ችግኞች ፀደቀላቸው?

## መፍትሄ

| የአንድ ቤት መቀነስ | የአስር ቤት መቀነስ |
|---|---|
| 68<br>−12<br>6<br>8 − 2 = 6 | 68<br>−12<br>56<br>6 − 1 =5<br>68 — 12 = 56. |



ስለዚህ 56 የቡና ችግኞች ፀድቆላቸዋል፡፡

## ምሳሌ 6

በአንድ ት/ቤት ውስጥ 85 ተማሪዎች የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተፈትነዉ 19ኞቹ ቢወድቁ ፈተናውን ያለፉት ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

| በአንድ ቤት ያሉትን መቀናናስ አይቻልም | አንድ 10 ተበደር/ሪ 10 አንዶች + 5 አንዶች =15 ይሆናሉ 7 አስሮችና 15 አንዶች ይኖረሃል/ይኖሪሻል | አንዶችን መቀነስ | የአስር ቤትን መቀነስ |
|---|---|---|---|
| 85<br>−19<br>?<br>5−9=? | 85<br>−19 | 85<br>−19<br>6<br>15−9=6 | 85<br>−19<br>66<br>7−1=6 |

85 - 19 = 66

ስለዚህ ያለፉት ተማሪዎች ብዛት 66 ይሆናሉ፡፡

## መልመጃ 1.3

1. የተሰጡትን ቁጥሮች ቀንስ/ሺ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. | ሠ. |
|---|---|---|---|---|
| 65<br>− 17 | 87<br>− 70 | 78<br>− 39 | 88<br>− 17 | 66<br>− 45 |

ረ. $\begin{array}{r}86\\-\underline{\ 14}\end{array}$ ሰ. $\begin{array}{r}49\\-\underline{\ 35}\end{array}$ ሸ. $\begin{array}{r}43\\-\underline{13}\end{array}$ ቀ. $\begin{array}{r}61\\-\underline{49}\end{array}$ በ. $\begin{array}{r}62\\-\underline{53}\end{array}$

2. የኮረና ቫይረስ ምርመራ ከተደረገላቸው 47 ሰዎች መካከል 33ቱ የበሽታው ምልክት ተገኘባቸው:: ከቫይረሱ ነፃ የሆኑ ሰዎች ብዛት ስንት ናቸው?

3. ሀ. 67 በስንት 37ን ይበልጣል? ለ. 68 በስንት ከ76 ያንሳል?

## ሐ. ባለ ሁለት ዲጂት ቁጥሮችን ማባዛት

**ሙሉ ቁጥሮችን በ2፣ በ3፣ በ4፣ በ5፣ በ6፣ በ7፣ በ8፣ በ9፣ እና በ10 ማባዛት**

### ምሳሌ 7

**የሚከተሉትን አብዛ/ዢ**

ሀ. 2 × 10 = ________ ለ. 3 × 18 = ________ ሐ. 4 × 12 = ________

መ. 5 × 10 = ________ ሠ. 6 × 15 = ________ ረ. 7 × 11 = ________

ሰ. 8 × 9 = ________ ሸ. 9 × 11 = ________

### መፍትሄ

ሀ. 2 × 10 = 10 + 10 = 20

ለ. 3 × 18 = 18 + 18 + 18 = 54

ሐ. 4 × 12 = 12 + 12 + 12 + 12 = 48

መ. 5 × 10 = 10 + 10 + 10 + 10 + 10 = 50

ሠ. 6 × 15 = 15 + 15 + 15 + 15 + 15 + 15 = 90

ረ. 7 × 11 = 11 + 11 + 11 + 11 + 11 + 11 + 11 = 77

ሰ. 8 × 9 = 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 +9 +9 = 72

ሸ. 9 × 11 = 11 + 11 + 11 +11 + 11 + 11 + 11 + 11 + 11 = 99

## መልመጃ 1.4

1. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች አብዛ/ዢ::

ሀ. 3 × 25 = _____ ለ. 7 × 14 = _____

ሐ. 4 × 24 = _____ መ. 8 × 12 = _____

ሠ. 5 × 13 = _____ ረ. 9 × 8 = ______

ሰ. 6 × 15 = _____ ሸ.10 × 9 = ______

2. የአንድ እርሳስ ዋጋ 5ብር ከሆነ የ15 እርሳሶች ዋጋ ስንት ይሆናል?

3. አንድ ሣጥን 10 ሎሚዎችን ይይዛል፡፡ 10 ተመሳሳይ ሣጥኖች ስንት ሎሚዎችን ይይዛሉ?

# 1.3 እስከ 10,000 ያሉ የ100 እና 1000 ብዜቶች

## ሀ እስከ 10,000 ያሉ የ100 ብዜቶች

### ትግበራ 1.2

እስከ 10,000 ያሉ የ100 ብዜቶች ዘርዝር/ሪ፡፡

### ምሳሌ 8

ሀ. 1×100 = 100 ለ. 3 ×100 = 300 ሐ. 5×100 = 500

መ. 2 ×100 = 200 ሠ. 4 ×100 = 400 ረ. 6 ×100 = 600

ከእነዚህ ምሳሌዎች የምንረዳው 100፣ 200፣ 300፣ 400፣ 500፣.... የ100 ብዜቶች መሆናቸውን ነው፡፡

**አስተውል/ይ**

**አንድ ሙሉ ቁጥር በ100 ሲባዛ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሁልጊዜ 0 ይሆናሉ፡፡**

### መልመጃ 1.5

1. በቁጥር ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ዘጠኝ መቶ ለ.ስድስት መቶ ሐ. ሰባት መቶ

መ. ሁለት መቶ ሠ. አምስት መቶ

2. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በ100 ብዜት በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 300=3×100 ለ. 700 ሐ. 500

መ. 800 ሠ. 400 ረ. 900

3. ስንት መቶዎች አሉት? በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ስራ/ሪ፡፡

ሀ. 500 = አምስት መቶ ለ. 800 ሐ. 600

መ. 300 ሠ. 700 ረ. 400

4. በፊደል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 500 ለ. 600 ሐ. 200

መ. 700 ሠ. 900 ረ. 800

5. ለበጎ አድራጎት ሥራ ዘጠኝ ሰዎች መቶ መቶ ብር ቢያዋጡ በአጠቃላይ ስንት ብር አዋጡ?

6. አስቴር ነጋዴ ናት፡፡ ከምታገኘው ትርፍ በቀን 100 ብር ብትቆጥብ በሳምንት ስንት ብር ትቆጥባለች?

## ለ. እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶች

### ምሳሌ 9

**ሀ.** 1×1000 = 1000 **ለ.** 2 ×1000 = 2000 **ሐ.** 3×1000 = 3000

**መ.** 4 ×1000 = 4000 **ሠ.** 5 ×1000 = 5000 **ረ.** 6 ×1000 = 6000

ከእነዚህ ምሳሌዎች የምንረዳው 1000፣ 2000፣ 3000፣ 4000፣ 5000፣... ፣10000 የ1000 ብዜቶች መሆናቸውን ነው፡፡

**አስተውል/ይ**

አንድ ሙሉ ቁጥር በ1000 ሲባዛ የአንድ ቤት፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሁልጊዜ 0 ይሆናል፡፡

### መልመጃ 1.6

1. በአሃዝ ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ስድስት ሺ ለ. ስምንት ሺ ሐ. ሶስት ሺ

መ. ሰባት ሺ ሠ. አራት ሺ ረ. አምስት ሺ

2. በፊደል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 7000 ለ. 8000 ሐ. 5000

መ. 3000 ሠ. 6000 ረ. 9000

3. አቶ ድርባ በየወሩ 1000 ብር የሚቆጥቡ ከሆነ በዘጠኝ ወራቶች ስንት ብር ይቆጥባሉ?

4. በአንድ ት/ቤት 1000 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ በአመቱ መጨረሻ እያንዳንዱ ተማሪ ሰባት ሰባት ችግኞች ቢተክሉ በአጠቃላይ ስንት ችግኞችን መትከል ይችላሉ?

## 1.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

### ትግበራ 1.3

1. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች በቤት ዋጋ በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 45 ለ. 324 ሐ. 8219

2. ቀጥሎ የተሰጡትን ቁጥሮች በቤት ዋጋ በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 1 አስር እና 7 አንዶች

ሐ. 7 ሺዎች 6 መቶዎች 6 አስሮች እና 2 አንዶች

### ምሳሌ 10

ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች በቤት ዋጋ በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 86 ለ. 573 ሐ. 3987

**መፍትሄ**

ሀ. $86 = 8 \times 10 + 6 \times 1$

ለ. $573 = 5 \times 100 + 7 \times 10 + 3 \times 1$

ሐ. $3987 = 3 \times 1000 + 9 \times 100 + 8 \times 10 + 7 \times 1$

**አስታውስ/ሽ**

በ3987 ውስጥ

- 3 ቁጥር በሺ ቤት ይገኛል:: ስለዚህ የቁጥሩ ቤት ዋጋ 3000 ይሆናል::
- 9 ቁጥር በመቶ ቤት ይገኛል:: ስለዚህ የቁጥሩ ቤት ዋጋ 900 ይሆናል::
- 8 ቁጥር በአስር ቤት ይገኛል:: ስለዚህ የቁጥሩ ቤት ዋጋ 80 ይሆናል::
- 7 ቁጥር በአንድ ቤት ይገኛል:: ስለዚህ የቁጥሩ ቤት ዋጋ 7 ይሆናል::

## መልመጃ 1.7

1. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች በቤት ዋጋ በመተንተን ፃፍ/ፊ፡፡

   ሀ. 49 ለ. 756 ሐ. 1209 መ. 8623

2. በአሃዝ ፃፍ/ፊ፡፡

   ሀ. 8 መቶዎች 4 አስሮች እና 9 አንዶች

   ለ. 6 መቶዎች 0 አስሮች እና 0 አንዶች

   ሐ. 7 መቶዎች 2 አስሮች እና 1 አንዶች

3. በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሰቀሱትን በቁጥር በመጻፍ አንብብ/ቢ፡፡

   ሀ. ጣይቱ በሰባት መቶ ዘጠኝ ብር ልብስ ገዛች

   ለ. ገዳ ት/ቤት ውስጥ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ተማዎች አሉ፡፡

   ሐ. ፋጡማ አራት ዶሮዎችን በዘጠኝ መቶ ዘጠና ስድስት ብር ሸጠች፡፡

4. በአረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሱትን በቁጥር በመጻፍ አንብብ/ቢ፡፡

   ሀ. የኮረና ቫይረስ በሁለት ሺህ አስራ ሁለት ዓ.ም በቻይና ሀገር ተገኘ፡፡

   ለ. አንድ ት/ቤት ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ የማጣቀሻ መጽሐፍትን በአንድ ጊዜ ገዛ፡፡

   ሐ. አርፋሴ አራት በጎችን በስምንት ሺህ ሁለት መቶ ብር ሸጠች፡፡

5. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች የቁጥር ቤት በመጠቀም ፃፍ/ፊ፡፡

| ቁጥሮች | ሺዎች | መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|---|---|
| 4672 | | | | |
| 5404 | | | | |
| 8540 | | | | |
| 9831 | | | | |

6. ከስር የተሰመረበት ቁጥር የቤት ዋጋ ስንት ነው?

   ሀ. 4<u>8</u>51 ለ. 74<u>6</u>5 ሐ. <u>4</u>985

መ. 9987 ሠ. 3084 ረ. 1649

# 1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸው ማስቀመጥ

## ሀ. ቀዳማይ እና ተከታይ

### ምሳሌ 11

ከ517 በአንድ የሚያንስ ቁጥር 516 ነው፡፡ ምክንያቱም 516 = 517-1 ስለሚሆን


| ቀዳማይ | የተሰጠ ቁጥር | ተከታይ |
|---|---|---|
| 516 | 517 | 518 |

**አስተውል/ይ**

1. ለማንኛውም ዜሮ ያልሆነ ሙሉ ቁጥር ሀ:"ሀ-1" የ "ሀ" ቀዳማይ ነው፡፡
2. ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፡ "ሀ + 1" የ"ሀ" ተከታይ ነው፡፡

ከ517 በአንድ የሚበልጥ 518 ነው፡፡ ምክንያቱም 518 =517 +1 ስለሚሆን

ከታች የተሰጡትን የቁጥር ጨረር በመመልከት ምሳሌዎችን አጥና/ኚ::




ሀ. 95 የ96 ቀዳማይ ነው፡፡ ለ. 96 የ95 ተከታይ ነው፡፡

ሐ. 100 የ101 ቀዳማይ ነው፡፡ መ. 104 የ103 ተከታይ ነው፡፡

### መልመጃ 1.8

ከታች ለተሰጡት ቁጥሮች ቀዳማይ እና ተከታዮቻቸውን በባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ

| | ቀዳማይ | ቁጥር | ተከታይ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | | 367 | |
| ለ. | | 732 | |
| ሐ. | | 659 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መ. | | 8993 | |
| ሠ. | | 9307 | |

## ለ. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

### ትግበራ 1.4

ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች አወዳድር/ሪ፡፡

ሀ. ከ1564 እና 145 የትኛው ይበልጣል?

ለ. ከ3259 እና 3167 የትኛው ያንሳል?

### ምሳሌ 12

1. 4869 እና 799 ቁጥሮችን አወዳድር/ሪ፡፡

**መፍትሄ**

4869 ከ 799 ይበልጣል፡፡ ምክንያቱም 4869 አራት ዲጂቶች ሲኖረው 799 ግን ሶስት ዲጂቶች አለው፡፡

ስለዚህ 4869>799 ወይም 799 <4869 ይሆናል፡፡

**አስተውል/ይ**

ብዙ ዲጂቶች ያለው ቁጥር ሁልጊዜ ትልቅ ቁጥር ነው፡፡

2. 9814 እና 9358 ቁጥሮችን አወዳድር/ሪ፡፡

**መፍትሄ**

| ቁጥር | የሺህ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|
| 9814 | 9 | 8 | 1 | 4 |
| 9358 | 9 | 3 | 5 | 8 |

9 = 9 ግን 8 > 3 ስለሆነ 9814 > 9358

**ማስታወሻ**

እኩል የዲጂት ብዛት ያላቸውን ቁጥሮች ስናወዳድር ከትልቁ የቤት ዋጋ ወደ ትንሹ ቁጥር/ከግራ ወደ ቀኝ/ እያወዳደርን እንሄዳለን፡፡ በትልቁ ቁጥር ቤት ውስጥ ያሉ ዲጂቶች እኩል ከሆኑ የሚቀጥለውን የቁጥር ቤት እናወዳድራለን፡፡

## መልመጃ 1.9

1. የ "<", " > " ¨ወይም " = " ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድር/ሪ፡፡

ሀ. 2634 _____ 1789 ለ 2105 _____ 2119

ሐ. 4703 _____ 998 መ 7209 _____ 6209

ሠ. 6543_____ 6534 ረ. 4589 _____ 4588

2. ቀጥሎ በተሰጠው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው አንድ ነጋዴ ለአምስት አመታት ስንዴ ወደ ውጪ ሀገር ልኳል::

| የተላከበት ዓ.ም | 2001 | 2004 | 2007 | 2010 | 2013 |
|---|---|---|---|---|---|
| የተላከው ስንዴ ብዛት /በኩንታል/ | 3,674 | 4,583 | 3,700 | 1,864 | 5,689 |

ሀ. ብዙ ኩንታል ስንዴ ወደ ውጪ ሀገር የተላከው በየትኛው ዓ.ም ነው?

ለ. ትራሽ ኩንታል ስንዴ ወደ ውጪ ሀገር የተላከው በየትኛው ዓ.ም ነው?

ሐ. ከ2001 እና 2007 በብዛት ስንዴ ወደ ውጪ ሀገር የተላከው በየትኛው ዓ.ም ነው?

## ሐ. እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

### ምሳሌ 13

ሀ. የተሰጡትን ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ፡፡

1369፣ 3657፣ 4281፣ 3979

**መፍትሄ**

1369 < 3657 < 3979 < 4281 ይሆናል፡፡

ለ. የተሰጡትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ፡፡

**መፍትሄ**

7658 > 7586 > 6899 > 6745 > 2345

ስለዚህ ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ስናስቀምጥ

7658፣ 7586፣ 6899፣ 6745፣ 2345 ይሆናል::

## መልመጃ 1.10

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ከትንሽ ከትልቅ ወደ በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 446፣ 492፣ 756፣ 919፣ 486፣ 502

ለ. 1469፣ 1909፣2878፣ 1999

ሐ. 492፣ 657፣ 482፣ 575፣ 209

መ. 5440፣ 4634፣8567፣ 8398

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. 250፣ 87፣ 376፣ 567

ለ. 8690፣ 4573፣ 7481፣ 9409፣ 7001

ሐ. 489፣ 768፣ 497፣ 658

መ. 6205፣ 6313፣ 6009፣ 6001፣ 6099

3. የተሰጠውን ሰንጠረዥ በመከተል ከ ሀ-ሰ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

| የተራሮች ስም | ጨለለቃ | ወንጪ | እንጦጦ | ጩቃላ | ዋዩ | ማልጉዶ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከፍታ/በሜትር/ | 3571 | 3387 | 3211 | 2989 | 3230 | 3390 |

ሀ. በሠንጠረዥ ውስጥ በተሰጡት የተራሮቹን ርዝማኔ ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጥ፡፡

ለ. በከፍታው ቅልቅ የሆነው ተራራ የትኛው ነው?

ሐ. በከፍታው በ3ኛ ደረጃ ላይ ያሚገኘው ተራራ የትኛው ነው?

መ. በከፍታው በጣም አነስተኛ የሆነው ተራራ የትኛው ነው?

ሠ. ከጩቃላ እና ዋዩ የበለጠ ከፍታ ያለው የቱ ነው?

ረ. ከዋዩ እና ማልጉዶ ዝቅተኛ ከፍታ ያለው የትኛው ነው?

ሰ. ከዋዩ ያነሰና ከጩቃላ የሚበልጥ ተራራ የትኛው ነው?

| ምዕራፍ 2 | 608 – 369 = ___<br>753 – 436 = ___ |
|---|---|
| እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ | |

## 2.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

**ትርጓሜ**
መደመር፡ ቁጥሮችን አንድ ላይ ማዋሄድ ነው፡፡ አንድ ላይ የሚደመሩ ቁጥሮች ተደማሪዎች ሲባሉ ውጤታቸው ደግሞ ድምር ይባላል፡፡

**ምሳሌ 1**

ደምር/ሪ ፤ 340 + 123 = 463

- 340 እና 123 → ተደማሪዎች
- 463 → ድምር

### 2.1.1 ባለ አንድ እና ባለ ሁለት ዲጂት ሙሉ ቁጥር ድምር ክለሳ

**ትግበራ 2.1**

ገልገሌ 27 አበቦች አላት፡፡ ጓደኛዋ ቢሊሴ ደግሞ 65 አበቦች ብትጨምርላት ገልገሌ ስንት አበቦች ይኖሯታል?

**ምሳሌ 2**

2 + 9 ቁጥሮችን በመነጣጠል እና በአስር አስር በመመደብ ደምር/ሪ::

**መፍትሄ**

2 + 9 = 1 +1 + 9 = 1 + 10= 11


## ምሳሌ 3

የቁጥር ቤትን በመጠቀም ቁልቁል ደምር/ሪ ::

14 + 22

**መፍትሄ**

ክዩቦችን በመጠቀም በቁጥር ቦታ ቁልቁል ደምር/ሪ::




## ምሳሌ 4

ገዳ ለትምህርት ቤቱ 37 የአፋን ኦሮሞ መጽሐፍት፣ 25 የእንግሊዝኛ መጽሐፍት እና 10 የሒሳብ መጽሐፍት አበረከተ፡፡ በአጠቃላይ ስንት መጽሐፍት አበረከተ?

**መፍትሄ**

**የተሰጠ፡ የአፋን ኦሮሞ መጽሐፍት ብዛት =37**

የእንግሊዝኛ መጽሐፍት ብዛት =25

የሒሳብ መጽሐፍት ብዛት =10

**የሚፈለግ፡ ጠቅላላ የመጽሐፍት ብዛት**

ስሌት፡ የአፋን ኦሮሞ የመጽሐፍት ብዛት + የእንግሊዝኛ የመጽሐፍት ብዛት + የሒሳብ መጽሐፍት የመጽሐፍት ብዛት

37 + 25 + 10 =72

ስለዚህ ገዳ ለትምህርት ቤቱ ያበረከተው የመጽሐፍት ብዛት 72 ነው፡፡

## መልመጃ 2.1

1. ከታች የተሰጡትን ቁጥሮች ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 16 + 13 ለ. 55 + 37 ሐ. 42 + 28

መ. 56 + 27 ሠ. 47 + 24

2. በአንድ ክፍል ውስጥ 36 ሴት ተማሪዎቸ እና 25 ወንድ ተማዎች አሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ውስጥ ስንት ተማሪዎች አሉ?

3. የተሰራው ምሳሌ በመከተል በሠንጠረዥ ውስጥ የተሰጠውን ባዶ ብታ ሙላ/ዪ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 23 | 75 | 30 | 48 | 37 |
| ለ | 42 | 20 | 46 | 22 | 65 |
| ሀ + ለ | 65 | | | | |

## 2.1.2 ባለ ሶስት ዲጂት ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

### ትግበራ 2.2

ቀጥሎ የተሰጡትን ቁጥሮች ደምር/ሪ፡፡

ሀ. 317 + 152 ለ. 263 + 728 ሐ. 278 + 556

መ. 488 + 436 ሠ. 815 + 556

### ሀ. የቁጥር ቤት ዋጋ በመጠቀም መደመር


**ምሳሌ 5**

ትላንትና ያተረፍኩት 215 ብር ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ 145 አተፈፍኩ፡፡ ትላንት እና ዛሬ ባጠቃላይ ስንት ብር አተረፍኩ?

**መፍትሂ**

215 +143?

ክዩቦችን በመጠቀም በቁጥሮች የቤት ዋጋ ቁልቁል መደር ነው፡፡




| 3 | 5 | 8 |
|---|---|---|
| 2 መቶ + 1 መቶ = 3መቶ | 1 አስር + 4 አስሮች = 5 አስሮች | 5 አንዶች + 3 አንዶች= 8 አንዶች |

ስለዚህ 215 + 143 = 358

| + | 2 | 1 | 5 |
|---|---|---|---|
| | 1 | 4 | 3 |
| | 3 | 5 | 8 |

## ለ. ቁልቁል መደመር

ባለ ሁለት ዲጂቶች ቁልቁል እንደ ደመርከው/ሽው ሁሉ ባለ ሶስት ዲጂቶችንም ቁልቁል መደመር ትችላለህ/ያለሽ፡፡ ከላይ በምስሉ ላይ እንዳስተዋላችሁት ያለቀሪ መደመር እንዴት እንደሚቻል ከታች የተሰጠውን ሠረጠረኘ ተመልከት/ቺ፡፡


## ምሳሌ 6

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቁልቁል ደምሪ/ሪ፡፡

ሀ. 146 + 537 ለ. 473 + 281

### መፍትሄ


ሀ. 146 + 537 ቀሪ ያለው የአንድ ቤት ነው፡፡




ስለዚህ 146+537 =683 ይሆናል፡፡

### መፍትሄ

ለ. 473+281 ቀሪ ያለው የአስር ቤት ነው፡፡




ስለዚህ 473+281 = 754 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 2.2

1.የሚከተሉትን ቁጥሮች ድምር አስላ/ይ፡፡

ሀ.

| | | | |
|---|---|---|---|
| + | 5 | 0 | 8 |
| | 3 | 7 | 1 |
| | | | |

ለ.

| | | | |
|---|---|---|---|
| + | 6 | 1 | 8 |
| | 3 | 5 | 2 |
| | | | |

ሐ.

| + | 2 | 8 | 0 |
|---|---|---|---|
| | 6 | 3 | 8 |
| | | | |

መ.

| + | 1 | 9 | 3 |
|---|---|---|---|
| | 4 | 6 | 9 |
| | | | |

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች በመደመር ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡

   ሀ. 341 + 282 + 172 = ___ ለ . 208 + 121 + 560 = ___

   ሐ . 143 + 92 + 233 = ___ መ. 160 + 308 + 940 = ___

   ሠ. 172 + 122 + 400 = ___ ረ. 234 + 256 + 175 = ___

2. ወ/ሮ ኢፍቱ በኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ መስከረም ወር 295 ብር እንደሁም ደግሞ በጥቅምት ወር 750 ብር ቢቆጥቡ በሁለቱ ወራት ስንት ብር ቆጠቡ?

3. የተሰጡትን ቁጥሮች በመደመር ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡

| ሀ | 123 | 755 | 230 | 548 | 271 |
|---|---|---|---|---|---|
| ለ | 342 | 200 | 467 | 121 | 656 |
| ሀ + ለ | | | | | |

## 2.2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**ትርጓሜ፤** መቀነስ፡ በሁለት ቁጥሮች መካከል ያለውን ልዩነት መፈለግ ማለት ነው፡፡ የሚቀነሰው ቁጥር ተቀናሽ ይባላል፡፡ የሚቀንሰው ቁጥር ደግሞ ቀናሽ ሲሆን የሚገኘው ውጤት ደግሞ ልዩነት ይባላል፡፡

**ምሳሌ 7**

| – | 58 | ተቀናሽ |
|---|---|---|
| | 32 | ቀናሽ |
| | 26 | ልዩነት/ብልጫ/ |

### 2.2.1 ባለ ሶስት ዲጂቶቹ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**ትግበራ 2.3**

በአንድ ት/ቤት ውስጥ 435 የ3ኛ ክፍል ተማዎች እና 323 የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ በሁለቱ ክፍሎች መካከል ያለው የተማሪዎች ብዛት ፈልግ/ጊ?



## ሀ. ያለ ብድር መቀነስ

### ምሳሌ 8

ጂቱ 328 ብር ይዛ ወደ ገበያ ሄደች፡፡ 215 ብር ወጪ ብታደርግ ስንት ብር በእጇ ላይ ይቀራል?




### መፍትሄ

ክዩቦችን በመጠቀም በቁጥር ቤት ዋጋ መቀነስ



| የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
|  3 |  2 |  8 |
| መቶዎች | አስሮች | 5 አንዶችን መቀነስ |
| | |  |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 2 | 8 |
| 2 | 1 | 5 |
| – | – | – |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 2 | 8 |
| 2 | 1 | 5 |
| | | 3 |

| መቶዎች | 1አስር መቀነስ | አንዶች |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 1 | 1 | 3 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 2 | 8 |
| 2 | 1 | 5 |
| | 1 | 3 |

| 2 መቶዎች መቀነስ | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
|  |  |  |
| 1 | 1 | 3 |

| መቶዎች | አስሮች | አንዶች |
|---|---|---|
| 3 | 2 | 8 |
| 2 | 1 | 5 |
| 1 | 1 | 3 |

## ለ. ቁልቁል መቀነስ

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3 | 2 | 8 |
| - | 2 | 1 | 5 |
| | 1 | 1 | 3 |

3 – 2 = 1    2 – 1 = 1    8 – 5 = 3

### ምሳሌ 9

768 – 534 ቁልቁል ቀንስ/ሽ፡፡

**መፍትሄ**

768 — 534 ያለ ብድር መቀነስ

| | | | |
|---|---|---|---|
| – | 7 | 6 | 8 |
| | 5 | 3 | 4 |
| | | | |

→

| | | | |
|---|---|---|---|
| – | 7 | 6 | 8 |
| | 5 | 3 | 4 |
| | 2 | 3 | 4 |

7 – 5 = 2    6 – 3 = 3    8-4 = 4

## ሐ. በብድር መቀነስ

### ምሳሌ 10

692 – 458 ቁልቁል ቀንስ/ሽ፡፡

**መፍትሄ**

692 — 458 ከአስር ቤት 1 ተበደር/ሪ

| | | | |
|---|---|---|---|
| – | 6 | 9 | 2 |
| | 4 | 5 | 8 |
| | | | |

→

| | | | |
|---|---|---|---|
| – | 6 | 9 | 2 |
| | 4 | 5 | 8 |
| | 2 | 3 | 4 |

6 – 4 = 2    8 – 5 = 3    10 +2=12, 12-8 =4

## ምሳሌ 11

425 − 286 ቁልቁል ቀንስ/ሽ።

| | | |
|---|---|---|
| − 4 | 2 | 5 |
| 2 | 8 | 6 |
| | | |

→

| | | | |
|---|---|---|---|
| − | 4 | 2 | 5 |
| | 2 | 8 | 6 |
| | 2 | 3 | 9 |

10 +5=15, 15 − 6 = 9

## መፍትሄ

425 − 286 1 ከመቶ ቤት ለአስር ቤት እና 1 ከአስር ቤት ለአንድ ቤት እንበደራለን።

| | | | |
|---|---|---|---|
| − | 4 | 2 | 5 |
| | 2 | 8 | 6 |
| | 1 | 3 | 9 |

3 − 2 = 1

←

| | | | |
|---|---|---|---|
| − | 4 | 2 | 5 |
| | 2 | 8 | 6 |
| | | 3 | 9 |

10 +1=11, 11 − 8 = 3

ስለዚህ 425 − 286 = 139

## መልመጃ 2.3

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ቀንስ/ሽ።

ሀ. 967 − 852 ለ. 742 − 62 ሐ. 458 − 213 መ. 264 − 52 ሠ. 6879 − 2436

2. የተሰጡትን ቁጥሮች በመበደር ቀንስ/ሽ።

ሀ. 327 − 118 ለ. 426 − 207 ሐ. 3144 − 1052 መ. 534 − 245 ሠ. 6255 − 4167

3. ኩሊ እና ሆርዶፋ ዶሮ ያረባሉ። ካራቡት 320 ዶሮዎች ውስጥ 135 ቢሸጡ ስንት ዶሮዎች ይቀራሉ?

4. ከታች የተሰጠውን ሠንጠረዥ ሙላ/ዪ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | 240 | 300 | 657 | 878 | 792 |
| ለ | 27 | 130 | 409 | 8 | 448 |
| ሀ−ለ | | | | | |

## 2.3 ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ ከሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍትሄ የምንፈልግበት ይሆናል፡፡ ለቃለት ፕሮብሌሞ መፍትሄ መፈለግ መቻል ከሂሳብ ትምህርት አላማ ሊዘነጋ የማይገባ ነው፡፡

### ምሳሌ 12

አንድ የጫማ ፋብርካ በ2012 ዓ.ም 4600 ጫማዎችን አመረተ፡፡ እንዲሁም በ2013 ዓ.ም ደግሞ 5200 ጫማዎችን አምርቶ ለገበያ አቀረበ፡፡

ሀ. በሁለቱ አመታት ውስጥ ያመረታቸው የጫማዎች ብዛት ስንት ናቸው?

ለ. በ2013 ዓ.ም የተመረቱት የጫማዎች ብዛት ከ2012 ዓ.ም ከተመረቱት በስንት ይበልጣል፡፡

### መፍትሄ

ሀ. የተሰጠ፡ በ2012 ዓ.ም የተመረቱት የጫማዎች ብዛት 4600 እና በ2013 ዓ.ም የተመረቱት የጫማዎች ብዛት 5200

የተፈለገው፡ በሁለቱ አመታት ውስጥ የተመረቱት የጫማዎች ብዛት

ስሌት፡ በሁለቱ ዓመታት የተመረቱት የጫማዎች ብዛት በመደመር እናገኛለን፡፡

$4600 + 5200 = 9800$ ይሆናል፡፡

ለ. በሁለቱ ዓመታት የተመተቱት የጫማች ብዛት በመቀነስ እናገኛለን፡፡

$6800 - 4600 = 2200$ ይሆናል፡

### ምሳሌ 13

አንድ ትምህርት ቤት በመጀመሪያ አት 536 ዴስኮች ገዛ፡፡ በቀጣይ አመት 287 ዴስኮችን ቢገዛ ትምህርት ቤቱ በሁለቱ አመታት ስንት ዴስኮችን ገዛ?

**መፍትሄ**

**የተሰጠ**: በመጀመሪያ አመት የተገዙት ዴስኮች ብዛት = 536

በሁለተኛ አት የተገዘት የዴስኮች ብዛት = 287

**የሚፈለግ**: በሁለቱ አመታት የተገዙት የዴስኮች ብዛት

**ስሌት፡** በሁለቱ ዓመታትየተገዙት የዴስኮች ብዛት በመደመር እናገኛለን፡፡

ይሂውም 536 + 287 = 823 ዴስኮች ይሆናሉ፡፡

## ምሳሌ 14

የቀይ መስቀል በዓል የሚከበርበት ቀን ለገቢ ማሳሰቢያ ከተዘጋጁት 5672 ኩፖኖች ውስጥ 5000 ተሽጠዋል፡፡ ያልተሸጡት የኩፖኖች ብዛት ስንት ናቸው?

**መፍትሄ**

የተሰጠ፡ የተዘጋጁት ኩፖኖች = 5672
የተሸጡት የኩፖኖች ብዛት = 5000

**የሚፈለገው** : ያልተሸጡት የኩፖኖች ብዛት

**ስሌት**: ከተዘጋጁት ኩፖኖች የተሸጡትን ኩፖኖች ብዛት በመቀነስ እናገኛለን፡፡

ይኸውም 5672-5000 = 672 ኩፖኖች ይሆናሉ፡፡

## መልመጃ 2.4

1. ኦዳ በጧት ተነስቶ 542 ሜትር በእግሩ ተጓዘ፡፡ከዚያም በመቀጠል 790 ሜትር በፈረስ ተጓዘ?
2. አንድን ስራ ትላንትና በ210 ደቂቃ ውስጥ ጨረስኩ፡፡ ዛሬ ግን በትኩረት ሰለስራው በ110 ደቂቃ ውስጥ ጨረስኩ፡፡ በሁለቱ ቀናት መካከል ያለው የደቂቃ ልዩነት ስንት ነው?
3. አንድ አውሮኘላን ለበረራ ሲነሳ 560 ሊትር ነዳጅ ነበረው፡፡ ተመልሶ ሲያርፍ ግን 240 ሊትር ነዳጁ ቢቀረው አውሮኘላኑ ምን ያህል ሊትር ነዳጅ ተጠቀመ?


4. የሁለት ክለቦች የእግር ኳስ ውድድር ግጥሚያ ለመመልከት የገቡት የተመልካቾች ብዛት በመጀመሪያ ሳምንት 341 በቀጣይ ሳምንት ደግሞ 742 ቢሆኑ

   ሀ. በሁለቱ ሣምንታት መካከል ያለው የተመካቾች ብዛት ልዩነት ፈልግ/ጊ፡፡

   ለ. በሁለቱ ሣምንታት የእግር ኳስ ውድድርን ለመመልከት የተገኙት የተመልካቾች ብዛት ስንት ናቸው?

5. አንዲት ተማሪ 240 ገጾች ካለው መጽሐፍ ውስጥ 165 ብታነብ ስንት ገጾች ይቀሯታል?

# ምዕራፍ 3




**እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት**

## 3.1 የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ዲጂት ቁጥር ማባዛት


### 3.1.1 ሙሉ ቁጥሮችን የማባዛት ክለሳ

**ትርጓሜ**

**ማባዛት፡** ተመሳሳይ የሆኑ የተደማሪዎች ድምር ነው፡፡

**ትግበራ 3.1**

1. ከዚህ በታች ላሉት ምስሎች “ ሀ ” ላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት “ለ” እና “ሐ”ን ስራ/ሪ፡፡



ሐ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ.. 4+4+4+4 =16<br>4 × 4 = 16 | ለ. | ሐ. |

2. ከዚህ በታች ያሉትን ተደማሪዎች በማባዛት ግለፅ/ጪ፡፡

ሀ. 5 + 5+ 5 + 5 + 5 + 5 =_____ ለ. 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 + 6 =______

ሐ. 8 + 8 + 8 + 8 + 8 + 8 =____ መ. 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9 + 9+9 +9 =____

## ምሳሌ 1

ከዚህ በታች በተሰጡት አራት ባለ አምስት ሳንቲም ምስሎች በአጠቃላይ ስንት ሳንቲሞችን እናገኛለን?



### መፍትሄ

20 ሳንቲሞችን እናገኛለን፡፡

ይህም $5 + 5 + 5 + 5 = 20$

ስለዚህ $4 \times 5 = 20$ ይሆናል፡፡


## ምሳሌ 2

በ $4 + 4 + 4 + 4 + 4 + 4$ ድምር ውስጥ 6 ተመሳሳይ ተደማሪዎች አሉ፡፡

ስለዚህ ድምሩ $4 + 4 + 4 + 4 + 4 + 4 = 6 \times 4 = 24$ ይሆናል፡፡

## ምሳሌ 3

ከዚህ በታች በተሰጠው ምስል ላይ ስንት ኪኒኒ እንደለ ሳንቆጥር ለማወቅ 3ን በ4 በማባዛት ማግኘት እንችላለን፡፡



## መልመጃ 3.1

1. ባዶ ቦታ ሙላ/ይ፡፡

ሀ. $6 \times 7 =$ __　　ለ. $7 \times 16 =$ ___　　ሐ. $8 \times$ __ $= 48$

መ. __ $\times 6 = 24$　　ሠ. $56 = 8 \times$ __

2. 1ኪ.ግ ቡና በ65 ብር ይሸጣል፡፡ 9ኪ.ግ ቡና በስንት ብር ይሸጣል?

3. ከዚህ በታች ያሉትን የማባዛት የካሬ ሰንጠረዥ በደብተርህ/ሽ ላይ በመገልበጥ በባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡

ሀ.

| × | 4 | 8 | 9 |
|---|---|---|---|
| 4 | | | |
| 8 | 32 | | |
| 9 | | | |

ለ.

| × | 3 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|
| 3 | | 18 | |
| 6 | | | |
| 7 | 21 | | |

4. አንድ ዘንቢል 10 እንቁላሎችን ይይዛል፡፡ ሦስት ተመሳሳይ ዘንቢሎች ስንት እንቁላሎችን ይይዛሉ?



እንቁላሎችን የያዘ ቅርጫት

## 3.1.2 የመቶ ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ዲጂት ሙሉ ቁጥር ማባዛት

### ትግበራ 3.2

2. ባዶ ቦታ ሙላ/ይ፡፡

ሀ. $4 \times 200 =$ ____ ለ. $2 \times 300 =$ ____

ሐ. $7 \times 100 =$ ____ መ. $3 \times 100 =$ ____

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ባላቸው የቤት ዋጋ በመተንተን አባዛ/ዢ፡፡

ሀ. 342 ለ. 823 ሐ. 905

### ምሳሌ 4

አንድ ሲኒ 100 ሚሊ ሊትር ይይዛል፡፡ ኦዳ በቀን ሶስት ሲኒ ቡና የሚጠጣ ከሆነ በቀን ስንት ሚሊ ሊትር ጠጥቶ ይውላል?



**መፍትሄ**

$3 \times 100 = 300$

ስለዚህ 300 ሚሊ ሊትር ቡና ጠጥቶ ይውላል ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ 5**

አንድ ነጋዴ በቀን 200 ብር አትርፎ ይውላል፡፡ በ5 ቀናት ውስጥ ስንት ብር ያተርፋል?

**መፍትሄ**

$5 \times 200 = 1000$

ስለዚህ 1000 ብር ያተርፋል፡፡

**መልመጃ 3.2**

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች አባዛ/ዢ፡፡

   ሀ. $100 \times 3$ ለ. $500 \times 2$ ሐ. $4 \times 200$

   መ. $3 \times 300$ ሠ. $2 \times 100$

2. አንድ በወተት ላሞች እርባታ የተሰማራ ተቋም በቀን 100 ሊትር ወተት ያከፋፍላል፡፡ ይህ ተቋም በ10 ቀናት ውስጥ ስንት ሊትር ወተት ያካፋፍላል?



# 3.2 ብዜታቸው 1000 በታች የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ዲጂት ማባዛት

## 3.2.1 ባለ ሁለት ዲጂት ቁጥሮችን በባለ 1 ዲጂት ማባዛት

### ትግበራ 3.3

1. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች አባዛ/ዢ፡፡


   ሀ. $31 \times 5$ ለ. $28 \times 7$ ሐ. $35 \times 5$ መ. $47 \times 3$ ሠ. $59 \times 8$

2. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች ቁልቁል አባዛ/ዢ፡፡

   ሀ. $\begin{array}{r} 63 \\ \underline{\times 2} \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 54 \\ \underline{\times 2} \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 16 \\ \underline{\times 6} \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 27 \\ \underline{\times 3} \end{array}$

## ሀ. ቁጥሮች ባላቸው የቤት ዋጋ በመተንተን የማባዛት ዘዴ

ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡




### መልመጃ 3.3

የሚከተሉትን ቁጥሮች ባላቸው የቤት ዋጋ በመተንተን አባዛ/ዢ፡፡

ሀ. 33 × 3 ለ. 32 × 3 ሐ. 97 × 8 መ. 88 × 7 ሠ. 89 × 9

## ለ. ያለአለኝታ ቁልቁል የማባዛት ዘዴ


**ምሳሌ 6**

21 × 3 ቁልቁል አብዛ/ዢ፡፡

**መፍትሄ**

$$\begin{array}{r} 21 \\ \times\ \ 3 \\ \hline 3 \times 20 = 60 \\ 3 \times 1 = 3 \\ \hline 60 + 3 = 63 \end{array}$$

ወይንም ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ማባዛት ይቻላል፡፡




## መልመጃ 3.4

የሚከተሉትን ቁትሮች ቁልቁል አባዛ/ዢ፡፡

ሀ. 34 × 2     ለ. 23 × 2     ሐ. 42 × 2     መ. 11 × 4     ሠ. 41 × 5


## ሐ. አለኝታ ያላቸውን ቁልቁል የማባዛት ዜዴ

### ምሳሌ 7

13 × 7ቁልቁል አባዛ/ዢ፡፡

**መፍትሄ**

ቀሪ ያለው የማባዛት ሂደት ነው፡፡




## መልመጃ 3.5

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል አባዛ/ዢ፡፡

   ሀ. 14 × 7     ለ. 13 × 5     ሐ. 24 × 4     መ. 12 × 6     ሠ. 27 × 3

2. ቱሊ 4 እስክሪብቶዎችን ገዛ፡፡ የአንዱ እስክሪብቶ ዋጋ 15ብር ቢሆን በአጠቃላይ በስንት ብር ገዛ?


## መ. ያለአለኝታ ቁልቁል የማባዛት ዘዴ

### ምሳሌ 9

71 × 4 ቁልቁል አብዛ/ገር፡፡

### መፍትሄ


አለኝታ ያለው ማባዛት ነው፡፡




### ምሳሌ 10

95 × 3 ቁልቁል አብዛ/ገር

መፍትሄ ፡ ይህ የማባዛት ሂደት 2 ግዜ አለኝታ ያለው ነው፡፡




## መልመ□ 3.6

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ቁልቁል አብዛ/ገር፡፡

   ሀ. 93 × 3 ለ. 41 × 5 ሐ. 63 × 2 መ. 85 × 9 ሠ. 74 × 8

2. አንድ የእግር ኳስ ቡድን 11 ተጨዋቾች አለው፡፡ 7 ቡድኖችን ለማቋቋም ስንት ተጫዋቾች ያስፈልጋሉ?
3. አንድ ሳጥን 24 ሳሙናዎችን ይይዛል፡፡6 ተመሳሳይ ሳጥኖች ስንት ሳሙናዎችን ይይዛል?

4. ቶላ አንድ ሰዓት ሰርቶ 80 ብር ያገኛል፡፡ 8 ሰዓት ሰርቶ ስንት ብር ያገኛል?

## 3.2.2 ባለ ሦስት ዲጂቶች ቁጥሮችን በባለ አንድ ዲጂት ቁጥር ማባዛት

### ትግበራ 3.4

1. የሚከተሉትን በቁጥሮች የቤት ዋጋ በመተንተን አባዛ/ዢ፡፡

ሀ. $131 \times 2$ ለ. $221 \times 4$ ሐ. $312 \times 3$ መ. $127 \times 3$ ሠ. $159 \times 5$

2. ከዚህ በታች ያሉትን ቁልቁል አባዛ/ዢ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 321 \\ \underline{\times\ 3} \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 404 \\ \underline{\times\ 2} \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 161 \\ \underline{\times\ 5} \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 327 \\ \underline{\times\ 3} \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 149 \\ \underline{\times\ 7} \end{array}$


### ሀ. ቁጥሮችን ባላቸው የቤት ዋጋ በመተንተን የማባዛት ዘዴ

#### ምሳሌ 9

በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 213 ተማሪዎች አሉ፡፡ እያንዳንዳቸው ሦስት ችግኞችን ቢተክሉ በጠቅላላው ስንት ችግኞችን ይተክላሉ?

**መፍትሄ**

አንዱ/ዷ ተማሪ ሦስት ችግኞችን ተከለ/ች ማለት በጠቅላላ $3 \times 213$ ተተከሉ ማለት ነው፡፡ በቁጥሮች የቤት ዋጋ ስተነተን $213 = 2x100 + 1x10 + 3x1$ ይሆናል፡፡



## ለ. ቁልቁል የማባዛት ዘዴ




### መልመጃ 3.7

1. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች አባዛ/ዢ፡፡

   ሀ. 201 × 7 ለ. 141 × 8 ሐ. 293 × 4 መ. 194 × 2 ሠ. 216 × 8

2. አንድ ደርዘን ደብተር በ246 ብር ይገዛል፡፡ 4 ደርዘን ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልጋል?



3. አንድ የውኃ ጣሳ 5 ሊትር ይይዛል፡፡125 ተመሳሳይ ጣሳዎች ስንት ሊትር ይይዛሉ?
4. አቶ ሊበኖ አርሶ አደር ናቸው:: የእርሻ መሬታቸው ከቤታቸው 500 ሜትር ይርቃል፡፡ □እርሻ መሬታቸው ጋር ደርሰው ቢመለሱ ምን ያህል ሜትር ተጓዙ?

## 3.3 ከማባዛት ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች

### ምሳሌ 11

አንድ የጭነት መኪና በ1 ሰዓት 65ኪ.ሜ ቢጓዝ በ7 ሰዓት ዉስጥ ስንት ኪ.ሜ ይጓዛል?

**መፍትሄ**

በ7 ሰዓት ዉስጥ የተጓዘዉን ርቀት ለማወቅ

(የተጓዘዉን ኪሎ ሜትር) × (በጉዞ ላይ የወሰደበት ሰዓት)= $65 \times 7 = 455$

ስለዚህ 455 ኪሎ ሜትር ተጓዘ ማለት ነዉ፡፡

## ምሳሌ 12

አንድ መጽሓፍ 120 ገጾች አሉት፡፡ ስምንት መጽሓፎች ስንት ገጾች አሏቸዉ?

**መፍትሄ**

ጠቅላላ የገጾቹን ብዛት ለማወቅ

(የአንድ መጽሓፍ የገጽ ብዛት) × (የመጽሓፎች ብዛት)= $120 \times 8 = 960$

ስለዚህ ባጠቃላይ ስምንቱ መጽሓፎች 60 ገጾች ይኖራቸዋል፡፡


## መልመጃ 3.8

1. የአንድ ሊትር የነዳጅ ዋጋ 9ብር ቢሆን የ15ሊትር ዋጋ ስንት ይሆናል?
2. አንድ መጽሐፍ በ235 ብር ይገዛል፡፡ አራት መጽሐፎች በስንት ብር ይገዛሉ?
3. አንድ ደስጣ 400 ወረቀቶችን ቢይዝ 2 ደስጣዎች ስንት ወረቀት ይይዛሉ?
4. አንድ መኪና በአንድ ጊዜ 250 የቤት ግንባታ ብሎኬቶችን ይጭናል፡፡ አራት ጊዜ ብመላላስ ስንት ብሎኬቶችን ይጭናል?

# ምዕራፍ 4

ሀ ÷ ለ =ሐ

24÷2=12



## እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል

## 4.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የማካፈል ክለሳ

### ትግበራ 4.1

አንዲት እናት ለ4 ልጆች 12 ከረሜላዎችን እኩል ብታካፍል ስንት ይደርሳል?




**ማካፈል ፡** ማካፈል ማለት የማብዛት ግልባጭ ሂደት ነዉ፡፡

### ምሳሌ 1



6 ብርቱካኖች ለ3 ልጆች እኩል ብናካፍላቸዉ ለእያንዳንዳቸዉ ስንትይዳርሳል?

**መፍትሄ**

ለእያንዳንዳቸዉ ሁለት ሁለት ይደርሳቸዋል፡፡

ይኸዉም 6 ÷ 3 = 2 ይሆናል፡፡

ስለዚህ 2 × 3 = 6 ይሆናል፡፡

ከዚህ በመነሳት ማካፈል የማብዛት ግልባጭ ነዉ እንላለን፡፡

**አስተዉል/ይ**

ሀ ÷ ለ = ሐ ከሆነ

ሀ - ተካፋይ

ለ - አካፋይ

ሐ - ድርሻ ይባላሉ፡፡

**መልመጃ 4.1**

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች አካፍል/ይ፡፡

ሀ. 9 ÷ 3    ለ. 16 ÷ 8    ሐ. 18 ÷ 3

መ. 12 ÷ 6    ሠ. 15 ÷ 5

2. 15 ኪዩቦች ለስንት ህጻናት እኩል ቢካፈል ሦስት ሦስት ሊደርሳቸዉ ይችላል?

## 4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለቀሪ ለ2 ማካፈል

### ትግበራ 4.2

1. 8 ዳቦዎችን ለ2 ሰዎች እኩል አካፍል፡፡ ለአንድ ሰዉ ስንት ይደርሳል?



2. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች አካፍል፡፡

ሀ. 4 ÷ 2    ለ. 6 ÷ 2    ሐ. 14 ÷ 2

መ. 16 ÷ 2    ሠ. 2 ÷ 2


ለሁለት ማካፈል ማለት የተሰጠንን ሁለት እኩል ቦታ መክፈል ማለት ነዉ፡፡

## ምሳሌ 2

ከዚህ በታች ያለዉ ምስል 8 ከዋክብቶችን 4 አባላት ባሉት ሁለት ቡድኖች መከፈላቸዉን ያሳያል፡፡ .

ይኸዉም 8 ÷ 2 = 4 ይሆናል፡፡

ስለዚህ ለ2 ማካፈል ማለት እኩል ሁለት ቦታ መክፈልን ያመለክታል፡፡



## ምሳሌ 3

10÷2 = 5 ማለት 10 ነገሮች እኩል 5 ቦታ መካፈላቸዉን ያሳያል፡፡

በሌላ መንገድ ማካፈል ማለት በድግግሞሽ መቀነስ ማለት ነዉ፡፡

ይህም ማለት 10 — 2 = 8  
8 — 2 = 6  
6 — 2 = 4  
4 — 2 = 2  
2 — 2 = 0 አምስት ጊዜ ስለቀነስን ድርሻ 5 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 4.2

1. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች አካፍል/ይ፡፡

   ሀ. 14 ÷ 2 ለ. 16 ÷ 2 ሐ.18 ÷ 2

   መ. 10 ÷ 2 ሠ. 20 ÷ 2

2. የሚከተሉትን በድግግሞሽ በመቀነስ አካፍል/ይ፡፡

   ሀ. 14 ÷ 2 ለ. 15 ÷ 3 ሐ. 12 ÷ 3

   መ. 10 ÷ 2 ሠ. 20 ÷ 5

3. ከዚህ በታች ያለዉን ሠንጠረዥ በደብተርህ/ሽ ላይ ከፃፍክ/ሽ በኃላ ለ2 የሚካፈሉትን ቁጥሮች ላይ አክብብ/ቢ፡፡ ከዚያ በኃላ በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ላይ ድርሻቸዉን ፃፍ/ፊ፡፡ ከታች የተሰጠውን ምሳሌ ተከተል፡፡

| ÷ | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለ2 | | | 2 | | | | | | | | | | | | | |

4. ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ በተሰጠው ምስሎች መሰረት ከተጠየቀው ጥያቄ በተሰጠው ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡



ሀ. ሰማያዊ ቀለም የተቀባው ለ2 ስታካፍል ______________

ለ. ጥቁር ቀለም የተቀባው ለ2 ስታካፍል ________________

ሐ. አርንጓዴ ቀለም የተቀባው ለ2 ስታካፍል _____________

## 4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ2 እና ለ10 ማካፈል

በ4.2 ርዕስ ሥር እንደተረዳሃዉ/ሽዉ ሙሉ ቁጥርን ለ2 ማካፈል ማለት እኩል ቦታ ማካፈል ማለት እነደሆነ ተመልክተሃል/ሻል፡፡ በዚህ ክፍል ዉስጥ ደግሞ በማሳደግ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ለ2 እና ለ10 እናካፍላለን፡፡

### 4.3.1 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ2 ማካፈል

#### ትግበራ 4.3

ጃገማና ደራርቱ በጋራ ከተከሉት ማንጎ ላይ 86 የማንጎ ፍሬ እኩል ተካፈሉ፡፡ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?



### ምሳሌ 4

ገመዳ 24 ብር አለዉ፡፡ ለሁለት ጓደኞቹ ሶርሳና ኩሜ እኩል ቢያካፍል ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

### መፍትሄ

24 ÷ 2 = 12 ይሆናል፡፡

### ምሳሌ 5

66 ÷ 2 = 33 ይሆናል፡፡

### ምሳሌ 6

[ ? ] ÷ 2 = 45

### መፍትሄ

ለ2 ተካፍሎ 45 የሚሰጥ ተካፋይ ቁጥር መፈለግ ማለት ነዉ፡፡

ስንት ይሆናል?

90ን ለ2 ሰዎች እኩል ብታካፍል 45 ይደርሳቸዋል፡፡

ስለዚህ በሳጥኑ ዉስጥ 90 እንፅፋለን፡፡

## መልመጃ 4.3

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች በማካፈል ባዶ ቦታ ሙላ/ይ፡፡

   ሀ. 26 ÷ 2 =___ ለ. 78 ÷ 2 =___ ሐ. 44 ÷ 2 =___

   መ. 58 ÷ 2 =___ ሠ. 52 ÷ 2=____ ረ. 98 ÷ 2 =___

   ሰ. 68 ÷ 2 =___ ሸ. 74 ÷ 2 =___ ቀ. 70 ÷ 2 =___

   በ. 22 ÷ 2=_____

2. ለ2 ተካፍለዉ የተሰጡትን ድርሻ የሚያስገኙ ተካፋይ ቁጥሮችን በሳጥን ዉስጥ ፃፍ/ፊ፡፡

   ሀ. [ ] ÷ 2 = 18 ለ. [ ] ÷ 2 = 11

   ሐ. [ ] ÷ 2 = 3 መ. [ ] ÷ 2 = 1

ሠ. ☐ ÷ 2 = 50 ረ. ☐ ÷ 2 = 28

ሰ. ☐ ÷ 2 = 36 ሸ. ☐ ÷ 2 = 46

ቀ. ☐ ÷ 2 = 20

## 4.3.2 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ10 ማካፈል

ሙሉ ቁጥሮችን ለአስር ማካፈል ማለት አንድን ነገር እኩል አስር ቦታ መክፈል ማለት ነዉ፡፡

### ትግበራ 4.4

90 ኪሎ ግራም ሩዝ ለ10 ሰዎች ስንት ስንት ኪሎግራም ይደረሳቸዋል?



### ምሳሌ 7

20 ሙዝ ለ10 ተማሪዎች ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

መፍትሄ፡ 20 ሙዝ እኩል ለ10 ተማሪዎች ብናካፍል

ለ1ተማሪ 2 ይደርሰዋል፡፡

ስለዚህ ሁለት ሁለት ይደርሳቸዋል ማለት ነዉ፡፡

ይኸዉም 20 ÷ 10 = 2 ይሆናል፡፡

### መልመጃ 4.4

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥሮች ድርሻቸዉን ፈልግ/ጊ፡፡

   ሀ. 50 ÷ 10 ለ. 70 ÷ 10 ሐ. 60 ÷ 10

   መ. 80 ÷ 10 ሠ. 90 ÷ 10

2. 50 ብር ለ10 ሰዎች ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

3. ርዝመቱ 40 ሳ.ሜ የሆነ ዱላ እርዝመታቸዉ ባለ10ሳ.ሜ የሆኑ ስንት ዱላዎች መቆራረጥ እንችላለን?

4. 100 ግራም ቡና በአስር አስር ለስንት ሰዎች ማካፈል ትችላለህ/ሽ?

# 4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ1 ማካፈል

## ትግበራ 4.5

አብዲ ያለዉን 30 ብር ለወንድሙ ሰጠዉ፡፡ የአብዲ ወንድም ስንት ብር ወሰደ? የአብዲ ወንድም ድርሻ ስንት ነዉ?

## ምሳሌ 8

25 ÷ 1 = 25 ይሆናል፡፡

**አስታዉስ/ሽ**

ማንኛዉም ሙሉ ቁጥር ለ1 ስታካፍል/ይ ድርሻዉ ከዚያዉ ተካፋይ ቁጥር ጋር እኩል ይሆናል፡፡

## መልመጃ 4.5

ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች በማካፈል ድርሻቸዉን ፈልግ/ጊ፡፡

ሀ. 5 ÷ 1 ለ. 7 ÷ 1 ሐ. 6 ÷ 1


መ. 80 ÷ 1 ሠ. 19 ÷ 1

# 4.5 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ3፣ ለ4፣ ለ5፣ ለ6፣ ለ7 ፣ለ8 እና ለ9 ማካፈል

## ሀ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ3 ማካፈል

## ትግበራ 4.6

15 ትናንሽ ሳጥኖች ለ3 ህፃናት እኩል ብታካፍል/ይ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?



### ምሳሌ 9

የአንድ እርሳስ ዋጋ 3ብር ነዉ፡፡ በ18ብር ስንት እርሳሶችን መግዛት ትችላለህ/ሽ?

### መፍትሄ

18ብር 3 እኩል ቦታ ክፈል/ይ፡፡ አንዱ ድርሻ ስንት ነዉ?

ይኸዉም 18 ÷ 3 = 6፡ በሌላ መንገድ 3 × 6= 18 ይሆናል፡፡

ስለዚህ 6 እርሳሶችን ትገዛለህ/ሽ ማለት ነዉ፡፡

### መልመጃ 4. 6

1. የሚከተሉትን አካፍል/ዪ

   ሀ. 21 ÷ 3 = ☐ ለ. 45 ÷ 3 = ☐ ሐ. 51 ÷ 3 = ☐

   መ. 54 ÷ 3 = ☐ ሠ. 60 ÷ 3 = ☐ ረ. 72 ÷ 3 = ☐

2. ገላኔ፣ ኩመላ እና ቡሳ የፍየል እርባታ ለይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ፡፡ በጋራ የነበራቸዉን 81 ፍየሎች እኩል ቢካፈሉ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

3. 99 ሜትር ርዝመት ያለዉ ገመድ በሦስት ብትከፋፍል ስንት ቦታ መክፈል ትችላለህ/ሽ?

4. 75ብር ለ3 ሰዎች ስንት ስንት ይደርሳል?

## ለ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ4 ማካፈል

### ትግበራ 4.7

አንድ መኪና በአንድ ሊትር ነዳጅ 4 ኪሎ ሜትር ይጓዛል፡፡ ይህ መኪና 40 ኪሎሜትር በስንት ሊትር ነዳጅ ሊጓዝ ይችላል?

### ምሳሌ 10

32 ችግኞች የሚተከሉበት እኩል ባለ4 መስመር መትከል ብንፈልግ በአንድ ረድፍ ላይ ስንት ችግኞችን መትከል ይቻላል?

### መፍትሄ

የችግኞቹን ብዛት በ4 ቦታ በመክፈል በአንድ መስመር ላይ የሚተከሉትን የችግኞቹን ብዛት ማግኘት ይቻላል፡፡

ይኸዉም 32 ÷ 4 = 8; በሌላ መንገድ 4 × 8 = 32 ይሆናል፡፡

ስለዚህ 8 ችግኞች በአንድ መስመር ይተከላሉ፡፡

## መልመጃ 4.7

1. ከዚህ በታች ያሉትን አካፍል/ይ፡፡

ሀ. 4 ÷ 4 = ☐ ለ. 24 ÷ 4 = ☐ ሐ. 80 ÷ 4 = ☐

መ. 36 ÷ 4 = ☐ ሠ. 60 ÷ 4 = ☐ ረ. 100 ÷ 4 = ☐

2. ለ92 ሊትር ዘይት ስንት ባለ4 ሊትር ዕቃ ያስፈልጋል?
3. የአንድ ላጲስ ዋጋ 4ብር ቢሆን በ64 ብር ስንት ላጲሶችን መግዛት ይቻላል?
4. አንድ መቀመጫ 4 ሰዎችን ያስቀምጣል፡፡ ለ76 ሰዎች ስንት ማቀመጫ ያስፈልጋል?

## ሐ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ5 ማካፈል

### ትግበራ 4.8

85 ሰዎችን ወንዝ ማዶ ለማሻገር 5 ጀልባ ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ጀልባዎች ብዛታቸዉ እኩል የሆነ ሰዎችን መያዝ ይችላሉ፡፡ አንድ ጀልባ ስንት ሰዎችን መያዝ ይችላል?



## ምሳሌ 11

95 ኪሎ ግራም ካሮት 5ኪሎ ግራም በሚይዙ ስንት ዘንቢሎች ማከፋፈል እንችላለን?

### መፍትሄ

በአጠቃላይ 95 ኪሎ ግራም ካሮት አንድ ዘንቢል በሚይዘዉ ኪሎ ግራም መጠን ማካፈል ይሆናል፡፡

ይኸዉም 95 ÷ 5 = 19

ስለዚህ 19 ዘንቢል ያስፈልጋል፡፡

## መልመጃ 4.8

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቁጥር አካፍል/ይ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. 10 ÷ 5 = ☐ | ለ. 55 ÷ 5 = ☐ |
| ሐ. 65 ÷ 5 = ☐ | መ. 80 ÷ 5 = ☐ |
| ሠ. 35 ÷ 5 = ☐ | ረ. 70 ÷ 5 = ☐ |

2. 5 ሰዎች በማህበር ተደራጅተዉ ያረቧቸዉን 100 በጎች እኩል ቢካፈሉ ስንት ስንት ይደርሳል?

3. በአንድ ክፍል ዉስጥ 90 መቀመጫዎች አሉ፡፡ በ5 እኩል ረድፍ ብንከፍል እያንዳንዱ ረድፍ ስንት መቀመጫዎችን ይይዛል?

4. 50ተማሪዎች እኩል አባል የያዘ 5 ቡድን መሥርተዉ አጭር ርቀት ሩጫ ለመወዳደር ፈለጉ፡፡ አንዱ ቡድን ስንት አባላት ይኖሩታል?


## መ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ6 ማካፈል

### ትግበራ 4.9


ስድስት ባለ2 ሊትር ዉሃ አንድ ደርዘን ይሆናል፡፡ 72 ደርዘን ስንት ሊትር ይሀናል?

## ምሳሌ 12

ከዚህ በታች ያለዉን ምስል 6 አባል ባላቸዉ ቡድኖች ክፈል፡፡



### መፍትሄ



18 ÷ 6 = 3 ከላይ ባለዉ ምስል ላይ የምንረዳዉ 18 ነገሮችን ስድስት ስድስት በሚይዝ 3 ቡድን እንከፍላለን፡፡ ይኸዉም ከዚህ በታች በምስሉ እንደቀረበዉ መመልከት ይቻላል፡፡

ስለዚህ በ6 ሦስት ቦታ ይካፈላል ማለት ነዉ፡፡

## መልመጃ 4.9

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች አካፍል/ይ፡፡

ሀ. 12 ÷ 6 = ☐ ለ. 54 ÷ 6 = ☐ ሐ. 78 ÷ 6 = ☐

መ. 48 ÷ 6 = ☐ ሠ. 66 ÷ 6 = ☐ ረ. 36 ÷ 6 = ☐

2. ተመሣሣይ የሆኑ 6 መኪኖች በአንድ ላይ 36 ጎማዎች አሏቸዉ፡፡ አንዱ መኪና ስንት ጎማዎች አሉት?

3. 90 ኪሎ ግራም ድንች ለ6 ሰዎች እኩል ብናካፍል ስንት ኪሎ ግራም ይደርሳቸዋል?

4. 42 ኪሎ ግራም ሙዝ ለ6 ሰዎች እኩል ብካፈል ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

## ሠ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ7 ማካፈል

### ትግበራ 4.10

በአንድ የመማሪያ ክፍል ዉስጥ 28 ህፃናት ይገኛሉ፡፡ እኩል ህፃናትን በያዘ ባለ7 ቡድኖች ብናቀናጅ አንዱ ቡድን ስንት ህፃናትን ይይዛል?



### ምሳሌ 13

አንድ ሣምንት 7 ቀናት አለዉ፡፡ 42 ቀናት ስንት ሣምንተት ይሆናሉ?

### መፍትሄ

በ42 ቀናት ዉስጥ ያሉትን ሣምንታት ለማግኘት በአንድ ሣምንት ዉስጥ ባሉት የቀናት ብዛት በማካፈል ነዉ፡፡ ይኸዉም $42 \div 7 = 6$ ይሆናል፡፡

ስለዚህ 42 ቀናት 6 ሣምንታት አሉት ማለት ነዉ፡፡

### መልመጃ 4.10

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች አካፍል/ይ፡፡

ሀ. $14 \div 7 =$ ☐ ለ. $49 \div 7 =$ ☐ ሐ. $77 \div 7 =$ ☐

መ. $56 \div 7 =$ ☐ ሠ. $21 \div 7 =$ ☐ ረ. $91 \div 7 =$ ☐

2. ኢፋ ከ7 ጓደኞቹ ጋር ሥራ ሰርተዉ ያገኙትን 84ብር እኩል ተካፈሉ፡፡ የአንድ ሰዉ ድርሻ ስንት ብር ነዉ?
3. አንድ ትምህርት ቤት 35 ክፍሎች አሉት፡፡ እኩል ክፍሎች ያላቸዉ 7 ህንፃዎች ቢኖሩት አንዱ ህንፃ ስንት ክፍሎች ይኖሩታል?
4. 7 ሰዎች 70ኪሎ ግራም ቅቤ እኩል ተካፈሉ፡፡ የአንድ ሰዉ ድርሻ ስንት ኪሎ ግራም ነዉ?

## ረ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ8 ማካፈል

### ትግበራ 4.11

40 ኳሶች አሉ፡፡ 8 ኳሶችን መያዝ የሚችሉ ስንት ሳጥኖች ያስፈልጋሉ?




### ምሳሌ 14

24 አፕሎችን ለ8 ተማሪዎች አካፍል፡፡ ለእያንዳንዳቸዉ ስንት አፕሎች ይደርሳቿል?

### መፍትሄ

የአፕሎቹን ብዛት በተማሪዎች ብዛት ብታካፍል/ይ ድርሻቸዉን ታገኛለህ/ሽ፡፡ ይኸዉም $24 \div 8 = 3$ ይሆናል፡፡ስለዚህ ለአንድ ተማሪ 3 አፕሎች ይደርሳሉ፡፡.

### መልመጃ 4.11

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች አካፍል/ይ፡፡

ሀ. $56 \div 8 =$ ☐ ለ. $72 \div 8 =$ ☐ ሐ. $16 \div 8 =$ ☐

መ. $32 \div 8 =$ ☐ ሠ. $8 \div 8 =$ ☐ ረ. $96 \div 8 =$ ☐

2. 64 ተማሪዎች በ8 እኩል አባላት ብናካፍል ስንት ቡድን እናገኛለን?
3. ከ80 ሜትር ያልተሰፋ ብትን የሱፍ ጨርቅ ላይ ስንት ባለ8 ሜትር ብትን የሱፍ ጨርቅ ማዉጣት እንችላለን?
4. 8 ሰዎችን የመጫን አቅም ባለዉ ሚኒባስ በአንድ ጊዜ 88 ሰዎችን ለማጓጓዝ ስንት ሚኒባሶች ያስፈልጋሉ?

## ሰ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለ9 ማካፈል

### ትግበራ 4.12

የኦሮሞ ሙዝዬም የባህል አዳራሽን ለመጎብኘት 72 ተማሪዎች ሄዱ፡፡
9 አስጎብኝዎች ቢኖሩ አንድ አስጎብኚ ብዛታቸዉ እኩል የሆነ ስንት ተማሪዎችን ያስጎበኛል?

### ምሳሌ 15

36 እንቁላሎች በእኩል ዘጠኝ ቦታ ብከፈሉ በአንዱ ቡድን ስንት ዕንቁላሎች ይኖራሉ?

**መፍትሄ**

$36 \div 9 = 4$

ስለዚህ በአንድ ቡድን 4 ዕንቁላሎች ይኖራሉ ማለት ነዉ፡፡

### መልመጃ 4.12

1. አካፍል/ይ፡፡

ሀ. $27 \div 9 =$ ☐ ለ. $72 \div 9 =$ ☐ ሐ. $18 \div 9 =$ ☐

መ. $45 \div 9 =$ ☐ ሠ. $9 \div 9 =$ ☐ ረ. $81 \div 9 =$ ☐


2. 90 ሰዎችን በስንት እኩል 9 አባላት ባላቸዉ ኮሚቴዎች መመደብ ትችላለህ/ሽ?

3. የአንድ መጽሓፍ ዋጋ 9 ብር ነዉ፡፡ በ63 ብር ስንት ተመሳሳይ መጽሓፎችን መግዛት ይቻላል?

# 4.6 ከቃላት ፕሮብሌሞች ጋር የተገናኙ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል

**ትግበራ 4.13**

30ሚሊ ሊትር የብርቱካን ጭማቂ እኩል ለ5 ህፃናት አካፍል። ለአንድ ህፃን ስንት ሚሊ ሊትር ይደርሳል?




## ምሳሌ 16

በሪሶ፣ዱሬቲና አያኔ 27 ችግኞችን በቤታቸዉ ግቢ ዙሪያ ተከሉ። ሶስቱም እኩል ብተክሉ እያንዳንዳቸዉ ስንት ችግኞችን ተከሉ?


### መፍትሄ

ሁሉም እኩል ስለተከሉ $27 \div 3 = 9$

ስለዚህ እያንዳንዳቸዉ ዘጠኝ ዘጠኝ ችግኞችን ተከሉ ማለት ነዉ።

## ምሳሌ 17

የተለያዩ ቀለማት ያላቸዉን 32 ካርዶች እኩል በስምንት ክፍለህ አስቀምጥ። ስንት ቡድን መመስረት ትችላለህ?



**መፍትሄ**


ጠቅላላ የካርዶቹን ብዛት በአንድ ቡድን ዉስጥ በሚገኙት ካርዶች ብዛት በማካፈል እናገኛለን፡፡

ይኸዉም $32 \div 8 = 4$ ይሆናል፡፡ ስለዚህ አራት ቡድኖችን እንገኛለን፡፡

## መልመጃ 4.13

1. አቶ መገርሣ 80 ፍየሎችን ለአራት ልጆቻቸዉ እኩል ብያካፍሉ ለእያንዳንዳቸዉ ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?
2. አንድ የወተት ላሞችን የሚያረባ ተቋም 48 ላሞች አሉት፡፡ ይህ ተቋም ላሞቹን እኩል ከፋፍሎ ወደ ሶስት የተለያዩ የሣር መስክ አሰማራቸዉ፡፡ በእያንዳንዱ የሣር መስክ ስንት ላሞችን ያሰማራል?
3. አቶ ደራራ ለ5 የጤፍ አጫጅ ሠራተኞች 95ብር ከፈሉ፡፡ እያንዳንዳቸዉ እኩል ብካፈሉ ስንት ይደርሳቸዋል?
4. ወ/ሮ ጂቱ ከሚያረባቸዉ በጎች መካከል ለእርድ የደረሱ 84 በጎች ለ6 ሆቴሎች አቀረቡ፡፡ ለእንዳንዱ ሆቴል ስንት በግ አቀረቡ?
5. አቶ ጉደታ በ4 ሰዓታት ዉስጥ 88 ችግኞችን ተከሉ፡፡ ወ/ሮ ቦንቱ ደግሞ በ5 ሰዓታት ዉስጥ 100 ችግኞችን ተከሉ፡፡ ከሁለቱም ሰዎች በአንድ ሰዓት ዉስጥ ብዙ ችግኞችን የተከለዉ ማነዉ?
6. 30 ኪሎ ግራም ቡና 5ኪሎ ግራም በሚይዝ ዕቃ ለማከፋፈል ስንት ዕቃዎች ያስፈልጉናል?

# ምዕራፍ 5





# የክፍልፋዮች መግቢያ

## 5.1 ስለ ግማሽ ፣ ሲሶ እና ሩብ የታወቁ ምሳሌዎችን በቁጥሮች መግለፅ


### የግማሾች፣ ሲሶዎች እና ሩቦች ክለሳ


ከዚህ በታች በቀረበዉ ምስል ላይ የተቀቡት ክፍሎች በክፍልፋይ ተገልጸዉ ይገኛሉ፡፡


| | | |
|---|---|---|
|  | $\frac{1}{2}$ | ሙሉዉ በሁለት እኩል ቦታ ተከፍሏል፡፡ በቀለም የተቀባዉ ግማሽ ነዉ፡፡ |
|  | $\frac{1}{3}$ | ሙሉዉ በሶስት እኩል ቦታ ተከፍሏል፡፡ በቀለም የተቀባዉ ሲሶ ነዉ፡፡ |
|  | $\frac{1}{4}$ | ሙሉዉ አራት እኩል ቦታ ተከፍሏል፡፡ በቀለም የተቀባዉ ሩብ ነዉ፡፡ |

## ትግበራ 5.1


1. የተቀባዉን ክፍል የሚገልፅ ክፍልፋይ ጻፍ/ፊ፡፡


ሀ.


ሐ.


ሠ.


ለ.



መ.



ረ.



2. ቀጥሎ ያሉትን በምስሎች ግለፅ/ጪ


ሀ. $\frac{1}{5}$ ለ. $\frac{1}{10}$


3. የተሰጡትን ክፍልፋዮች በስዕሉ ላይ በመቀባት አሳይ/ዪ፡፡


ሀ.

$\frac{3}{4}$

ሐ.

$\frac{2}{4}$

ሠ.

$\frac{2}{3}$

ለ.

$\frac{1}{6}$


መ.

$\frac{1}{4}$

ረ.

$\frac{3}{8}$

## 5.2 ከ $\frac{1}{10}$ እስከ $\frac{1}{2}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች

### ሀ. አሃዳዊ ክፍልፋዮችን መለየት

ከዚህ በታች የቀረበዉን ምስል ተመልከት/ቺ፡፡



ከአራቱ የተቀባዉ አንዱ ብቻ ነዉ፡፡

ይህም በክፍልፋይ ሲገለፅ $\frac{1}{4}$ ይሆናል፡፡

ሲነበብ አንድ አራተኛ እንላለን፡፡

## ትግበራ 5.2

የመገርሳ አባት አንድ ብርቱካን አራት እኩል ቦታ አካፈለ፡፡ አንድ ክፋይ ለጫላ ሁለተኛዉን ክፋይ ለደራርቱ ሶስተኛዉን ክፋይ ለባይሳ አራተኛዉን ክፋይ ለፈይኔ የሚሰጥ ቢሆን

ሀ. ጫላ ያገኘዉን በክፍልፋይ ጻፍ/ፊ፡፡


ለ. ደራርቱ ያገኘችዉን በክፍልፋይ ጻፍ/ፊ፡፡

ሐ. ባይሳ ያገኘዉን በክፍልፋይ ጻፍ/ፊ፡፡


መ. ፈይኔ ያገኘችዉን በክፍልፋይ ጻፍ/ፊ፡፡

## መልመጃ 5.1

1. ከዚህ በታች በቀረቡት ምስሎች ላይ የተቀቡትን ክፍል በክፍልፋይ ፃፍ/ፊ፡፡




2. የተሰጡትን ክፍልፋዮች በምስላቸዉ ላይ በመቀባት አሳይ/ዪ፡፡





3. የተሰጡትን ክፍልፋዮች በቃላት ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. $\frac{1}{2}$ ለ. $\frac{1}{3}$ ሐ. $\frac{1}{4}$ መ. $\frac{1}{7}$ ሠ. $\frac{1}{10}$

4. ከዚህ በታች የቀረቡትን በቁጥር ግለፅ፡፡
   ሀ. አንድ አምስተኛ ለ. አንድ ስድስተኛ ሐ. አንድ ዘጠነኛ

5. በተሰጡ ምስሎች ላይ የተቀባዉን ክፍል የሚወክሉ ክፍልፋዮች በቀኝ በኩል በሚገኘዉ ባዶ ቦታ ላይ ፃፍ፡፡




## ለ. የክፍልፋዮች ላዕል እና ታህት

**አስተዉል/ይ**

$\frac{1}{4}$ ዉስጥ 1 ላዕል ወይስ 4 ታህት ይባላል፡፡

## መልመጃ 5.2

1. የእያንዳዳቸዉን ክፍልፋዮች ላዕል እና ታህት ክፍልፋዮች ለይተህ ጻፍ/ፊ፡፡
   ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{1}{6}$ ሐ. $\frac{1}{7}$
   መ. $\frac{1}{8}$ ረ. $\frac{1}{9}$ ሠ. $\frac{1}{10}$
2. ከተሰጡት ክፍልፋይ ዉስጥ ላዕል ወይስ ታህት ይበልጣል?

ሀ. $\frac{1}{10}$ ለ. $\frac{1}{7}$ ሐ. $\frac{1}{5}$ መ. $\frac{2}{3}$

3.ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተሰጠውን ቁጥር ትክክለኛውን መልስ በባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡


| ክፍልፋይ | $\frac{1}{9}$ | | | $\frac{1}{6}$ | $\frac{1}{8}$ |
|---|---|---|---|---|---|
| ላዕል | 1 | 1 | 1 | | |
| ታህት | | 7 | 4 | | |


## 5.3 የሙሉ ቁጥሮች ግማሾች እና ሩቦች

### ሀ. ግማሽ

አንድ ሙሉ ቁጥር እኩል ቦታ ሲከፈል የሚገኘዉ ድርሻ ግማሽ ይባላል፡፡

**ምሳሌ 1**






10 ÷ 2 = 5 ስለዚህ 5 የ10 ግማሽ ነዉ፡፡

12 ÷ 2 = 6 ስለዚህ 6 የ 12 ግማሽ ነዉ፡፡

### ለ.ሩብ

የሙሉ ቁጥር ሩብ ማለት አንድ ሙሉ ቁጥር አራት እኩል ቦታ በማካፈል የሚገኘዉ ዉጤት ማለት ነዉ፡፡.

**ምሳሌ 2**



12 ÷ 4 = 3 ስለዚህ 3 የ12 ሩብ ነዉ፡፡

**መልመጃ 5.3**

1. ለተሰጡት ቁጥሮች ግማሽ ፈልግ/ጊ፡፡

ሀ. 4 ለ. 6 ሐ. 8 መ. 14 ረ. 36 ሠ. 88

2. ለእያንዳንዱ ቁጥሮች ሩባቸዉን ፈልግ/ጊ፡፡

ሀ. 4 ለ. 16 ሐ. 24 መ. 28 ረ. 36 ሠ. 52

3. የጫልቱ ቤተሰብ 20 የቤት እንስሳት አላቸዉ፡፡ ከእነዚህ የቤት እንስሳት ዉስጥ ግማሾቹ በጎች ቢሆኑ የበጎቹ ብዛት በክፍልፋይ ስንት ይሆናል?

4. ኢሊሊ 24 ሙዞችን ከገበያ ገዛች፡፡ ሩቡ ስንት ነዉ?



5. የ64 ግማሽ ስንት ነዉ?

6. የ80 ሩብ ስንት ነዉ ?

## 5.4 አቻ ክፍልፋዮችን ማሳየት

### ትግበራ 5.3

ጫላ እና ጫልቱ እኩል የሆኑ ብርቱካኖችን ከዚህ በታች እንደቀረበዉ ቆራርጠዉ በሉ፡፡

| | |
|---|---|
|  | ጫላ የተሰጠዉን ብርቱካን ሁለት እኩል ቦታ ከፍሎ አንዱን በላ፡፡ |
|  | ጫልቱ የተሰጣትን ብርቱካን አራት እኩል ቦታ ከፍላ ሁለቱን በላች፡፡ |

ሀ. ጫላ የበላዉን በክፍልፋይ ግለፅ፡፡


ለ. ጫልቱ የበላችዉን በክፍልፋይ ግለፅ፡፡

ሐ. ከጫላ እና ጫልቱ ማን ትልቅ በላ?

መ. $\frac{1}{2}$ እና $\frac{2}{4}$ እኩል ናቸዉ ?

## ምሳሌ 3

በቀረቡት ስእሎች ላይ የተቀቡት ክፍሎች በክፍልፋይ ተገልፀዉ ይገኛሉ፡፡





የተቀቡት የስዕል ክፍሎች  እኩል ናቸዉ፡፡

ይህም $\frac{1}{3} = \frac{2}{6} = \frac{3}{9}$

ስለዚህ $\frac{1}{3}$፣ $\frac{2}{6}$ እና $\frac{3}{9}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸዉ፡፡.

## ምሳሌ 4




የተቀቡት ክብ ክፍሎች እኩል ናቸዉ፡፡


ይኸዉም $\frac{1}{2} = \frac{2}{4} = \frac{3}{6} = \frac{4}{8}$ ይሆናል፡፡

ስለዚህ $\frac{1}{2}$፣ $\frac{2}{4}$፣ $\frac{3}{6}$፣ $\frac{4}{8}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸዉ፡፡



## መልመጃ 5.4

1. በቀረቡት ምስሎች ላይ የተሰጡትን አቻ ክፍልፋዮች በመቀባት ግለፅ/ጪ፡፡




ሀ. $\frac{1}{3} = \frac{2}{6}$ በምስሎቹ ላይ ቀባ/ቢ፡፡






ለ. $\frac{1}{4} = \frac{2}{8}$ በምስሎቹ ላይ ቀባ/ቢ፡፡

2.በተሰጡት ምስሎች ላይ የተቀቡትን ክፍሎች በክፍልይ ግለጽ/ጪ፡፡

ሀ.  ______  ______  ______

ለ.  ______  ______  ______

# ምዕራፍ 6





# ፓተርኖች

## 6.1 እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖችን መለየት

### የቡድን ሥራ 6.1

1. በከተማ ዉስጥ የእግረኞች የመኪና መንገድ ማቋረጫ ምልክት (ዜብራ) አስተዉለሃል/ሻል? ፓተርኑ የተሠራበት የቀለም አቀባብ ግለፅ/ጪ?




2. የትራፊክ መብራት አይተህ/ሽ ታዉቃለህ/ሽ? ቀይ መብራት ሲበራ ምን ለማመልከት ነዉ? አራንጓዴና ቢጫስ? ተወያዩበት፡፡
3. የባህል አልባሳትን ታዉቃለህ/ሽ? የተሰራበት ቀለም ፓተርን ይፈጥራል ወይንስ አይፈጥርም?

### ትግበራ 6.1

ከዚህ በታች የተሰጡት ፓተርኖች የሚደጋገም ወይንም የሚጨምር መሆናቸዉን ለይ/ዩ፡፡

1. △ ▽ △ ▽ △ ▽ △ …
2. ♡ □ ♡ ♡ □ ♡ ♡ ♡ □ …
3. ■ □ ■ ■ □ ■ ■ ■ □ …
4. 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ …
5. 1፣ 2፣ 1፣ 2፣ 1፣ 2፣ . . .
6. 1፣ 3፣ 5፣ 7፣ . . .

**ትርጓሜ**

**ፓተርን፡-** የአንድ ነገር ስብስብ ወይም ቁጥሮች በቅደም ተከተል የምናስቀምጥበት ህግ ወይም የተለየ መንገድ ነዉ።እያንዳንዳቸዉ በፓተርኑ ዉስጥ የሚገኙት ነገሮች ወይም ቁጥሮች ቁሞች ይባላሉ።

## የሚደጋጋም ፓተርን

**ትርጓሜ**

የሚደጋገም ፓተርን ማለት ቁሞቹ የፓተርኑን ህግ ጠብቀዉ ደጋግመዉ የሚመጡ ከሆነ ነዉ።

### ምሳሌ 1

ከዚህ በታች የተሰጡት ፓተርኖች የተደጋጋሙ መሆናቸዉን ግለፅ/ጪ።

ሀ. ○ ○ ○ □ ○ ○ ○ □ …

ለ. 4፣ 4፣ 4፣ 7፣ 4፣ 4፣ 4፣ 7፣ …

### መፍትሄ

ሀ. ይህ ፓተርን ነዉ። ከእያንዳንዱ ሶስት ተከታታይ የክብ ምስሎች በኋላ በድግግሞሽ የካሬ ምስል ይገኛል።

ለ. ይህ ፓተርን የሚደጋጋም ነዉ። ከእያንዳንዱ ሶስት ተከታታይ 4 ቁጥር በኋላ በድግግሞሽ 7 ቁጥር ይገኛል።

ከዚህ በታች የተሰጡት እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖች መሆናቸዉን ግለፅ/ጪ፡፡

ሀ. ☺△☺△△☺ …

ለ. 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5 …

**መፍትሄ**

ሀ. በእያንዳንዱ የፊት ምስል መካካል ጎነ ሶስቱ በአንድ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ ይህ ፓተርን እየጨመረ የሚሄድ ፓተርን ነዉ፡፡

ለ. የተሰጠዉ የመቁጠሪያ ቁጥር ነዉ፡፡ በአንድ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ ይህ ፓተርን እየጨመረ የሚሄድ ፓተርን ነዉ፡፡

**መልመጃ 6.1**

ከዚህ በታች የሉትን ፓተርኖች በማስቀጠል የሚደጋገም ፓተርን ወይም እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖች በማለት ለይ/ዪ፡፡

1. □ ⬠ □ ⬠ □ ⬠ ______፣______፣ ____
2. ♡ ○ ♡ ♡ ○ ♡ ♡ ♡ ○ ______፣______፣ ____
3. ሀ ለ ሐ ሀ ለ ሐ ሀ ለ ሐ ሀ ______፣______፣ ____
4. ■ ● ▲ ■ ● ▲ ■ ● ______፣______፣ ____
5. 2፣ 4፣ 6፣ _____፣ _____፣_____


## 6.2 እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖችን ማስቀጠል

### ትግበራ 6.2

የተሰጡትን ምስሎች በመመልከት እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖችን ለማስቀጠል ባዶ ቦታ አሟሉ፡፡

1. ♥♥ ♥♥♥♥ ♥♥♥♥♥♥ _______
2. △○ △○○ △○○○ _______

3. ምስል 1 ምስል 2 ምስል 3 ምስል 4




____

4. 8፣ 7፣ 6፣ 5፣___፣____፣____፣___

## ምሳሌ 3

ከዚህ በታች የተሰጡትን እየጨመሩ የሚሄዱ የምስል ፓተርኖችን አስቀጥል/ይ።

1.  ________


2.  ________

### መፍትሄ

ከላይ የተሰጡት እየጨመሩ የሚሄዱ ፓተርኖች ናቸዉ።

የቅደም ተከተሉ ሁኔታ በአንድ እየጨመረ የሚሄድ ነዉ።


ስለዚህ ቀጥሎ የሚመጡት ቁሞች፤


1. 

2. 

## መልመጃ 6.2

ከዚህ በታች ለተሰጡት ፓተርኖች ቀጥሎ የሚመጣዉን አባል ገምት/ቺ።

1.  ________

2.  ________

3.  ________

4. ★ ★ ★ ★    ★ ★ ★ ★ ______
★ ★ ★ ★

# 6.3 በሚደጋገሙ እና እየጨመሩ በሚሄዱ ፓተርኖች ዉስጥ ርቀዉ የሚገኙ አባሎችን መገመት

## ትግበራ 6.3

1. ከዚህ በታች በተሰጡት ፓተርኖች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ:: ☺☺☺△☺☺☺△☺☺☺

   ሀ. ቀጥሎ የሚመጣዉ ቅርፅ የትኛዉ ነዉ?

   ለ. ፓተርኑ የሚቀጥል ከሆነ በ16ኛ ላይ የሚመጣ ቅርፅ የቱ ነዉ?

   ሐ. ጎነ ሦስት ምስል በየትኞቹ የመቁጠሪያ ቁጥሮች ላይ ይመጣል?

   መ. ፓተርኑ እስከ 20 ቢቀጥል ስንት ጎነ ሦስት እናገኛለን?

2. 100፣ 200፣ 300፣ 400፣ … እየጨመረ የሚሄድ ፓተርን ነዉ::

   ሀ. አምስተኛዉ ቁሞ ስንት ይሆናል?

   ለ. አስረኛዉ ቁሞ ስንት ይሆናል?

   ሐ. መቶኛዉ ቁሞ ስንት ይሆናል?

### ምሳሌ 4

በፓተርን 3፣ 6፣ 9፣ … ዉስጥ የሚከተሉትን ፈልግ/ጊ::

**ሀ.** አስረኛዉ ቁሞ

**ለ.** ሰላሰኛዉ ቁሞ

### መፍትሄ

ይህ እየጨመረ የሚሄድ ፓተርን ነዉ:: በሦስት ሦስት እየጨመረ ይሄዳል::

አንደኛዉ ቁሞ $= 3 \times 1 = 3$

ሁለተኛዉ ቁሞ $= 3+3 = 3 \times 2 = 6$

ሦስተኛዉ ቁሞ $= 3+3+3 = 3 \times 3 = 9$

አራተኛዉ ቁሞ $= 3 \times 10 = 30$

ሰላሰኛዉ ቁሞ $= 3 \times 30 = 90$

## መልመጃ 6.3

1. ከታች ያለዉ ሠንጠረዥ የዉሾችና እግሮቻቸዉ ብዛት የሚያሣይ ፓተርን ነዉ፡፡

| የዉሾች ብዛት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የዉሾች እግር ብዛት | 4 | 8 | 12 | 16 | 20 |

በተሰጠዉ ሠንጠረዥ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

ሀ. የዉሻ ቁጥር በአንድ ከጨመረ የዉሻ እግሮች ብዛት በስንት ይጨምራል?

ለ. ይህ ፓተርን እየጨመረ የሚሄድ ከሆነ አስር ዉሾች ስንት እግሮች ይኖራቸዋል?

ሐ. መቶ ዉሾች ስንት እግሮች ይኖራቸዋል?

2. ኢፋ 23 ሙዞችን ገዝቶ ከቤት አለዉ፡፡ በቀን ሦስት ሙዞችን ይበላል፡፡ ከ7 ቀናት በኃላ ስንት ሙዞች ይቀሩታል?

3. አቶ ዲናግዴ መኖሪያ ቤቱን ለመሸጥ ወሰነ፡፡ ቤቱ ሳይሸጥ ከቆየ በየሳምንቱ 100 ብር ይቀንስበታል፡፡ በ11ኛዉ ሳምንት በስንት ብር ይቀንሳል?

# 6.4 ከፓተርን ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች

### ምሳሌ 5

የመደመር ሠንጠረዡን ተመልከት/ቺ፡፡

የመደመር ሠንጠረዥ ላይ እየጨመረ ባለዉ ፓተርን ላይ በመመርኮዝ:-

**ሀ.** በእያንዳንዱ አግድምና ቁልቁል ያሉት ቁጥሮች በስንት እየጨመሩ ይሄዳሉ?

**ለ.** ከግራ ወደ ቀኝ ባለዉ ሰያፍ ላይ ያሉ ቁጥሮች በስንት እየጨመሩ ይሄዳሉ?

| + | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 0 | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 2 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 3 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 4 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 5 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |

**መፍትሄ**

ሀ. በእያንዳንዱ አግድምና ቁልቁል በአንድ ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል፡፡

ለ. ከግራ ወደ ቀኝ ባለዉ ሰያፍ ላይ ያሉ ቁጥሮች በሁለት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

## ምሳሌ 6

ከታች ያለዉ የወር ካላንደር እየጨመረ የሚሄድ ፓተርን ያሣያል፡፡ በዚህ ሠንጠረዥ ላይ በመመርኮዝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

ሀ. በእያንዳንዱ አግድም ላይ ቁጥሮች በስንት እየጨመሩ ይሄዳሉ?

ለ. በእያንዳንዱ ቁልቁል ላይ ቁጥሮች በስንት እየጨመሩ ይሄዳሉ?

ሐ. ከግራ ወደ ቀኝ ባለዉ ሰያፍ ላይ ቁጥሮች በስንት ይጨምራሉ?

መ. ከቀኝ ወደ ግራ ባለዉ ሰያፍ ላይ ቁጥሮች በስንት ይጨምራሉ?

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | | |

**መፍትሄ**

ሀ. በእያንዳንዱ አግድም ላይ ቁጥሮች በአንድ እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

ለ. በእያንዳንዱ ቁልቁል ላይ ቁጥሮች በሰባት እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡

ሐ. ከግራ ወደ ቀኝ ባለዉ ሰያፍ ላይ ቁጥሮች በስምንት ይጨምራሉ፡፡

መ. ከቀኝ ወደ ግራ ባለዉ ሰያፍ ላይ ቁጥሮች በስድስት ይጨምራሉ፡፡

## መልመጃ 6.4

1. ጫሊ 100 ብር አለዉ፡፡ በየሣምንቱ 10 ብር እየቆጠበ ቢጨምርበት ከ10 ሣምንታት በኃላ ስንት ብር ይኖረዋል?

2. ለሜሣ ልደቱን ለማክበር ጓደኞቹን ጠራቸዉ፡፡ አራት አግዳሚ ጠረጴዛዎች እያንዳንዳቸዉ 5 ሰዎች መያዝ የሚችሉትን አዘጋጀ፡፡ የተዘጋጁት ጠረጴዛዎች ስንት መያዝ ይችላሉ?

3. ገነሞ ቀይ፣ ሰማያዊና ነጭ ቀለሞችን በቅደም ተከተል ተጠቅሞ ሹራብ ሠራ፡፡ በሹራቡ ላይ የተጠቀመባቸዉ ቀለማት በዚሁ ፓተርን ከቀጠሉ፡-

ሀ. በ7ተኛ ላይ የሚገኘዉ ቀለም የትኛዉ ይሆናል?

ለ. ነጭ ቀለም በየትኞቹ የመቁጠሪያ ቁጥሮች ላይ ይመጣል?

ሐ. ቀይ ቀለም በየትኞቹ የመቁጠሪያ ቁጥሮች ላይ ይመጣል?

4.ከዚህ በታች በተሰጠዉ ሠንጠረዥ ላይ እየጨመረ የሚሄደዉን ፓተርን ለይ/ዪ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | 4 | 6 | 8 | 10 |
| 12 | 14 | 16 | 18 | 20 |
| 22 | 24 | 26 | 28 | 30 |
| 32 | 34 | 36 | 38 | 40 |
| 42 | 44 | 46 | 48 | 50 |

# ምዕራፍ 7

| አፋን ኦሮሞ |  |
| --- | --- |
| እንግሊዘኛ |  |
| … | … |

# የዳታ አያያዝ

## 7.1 የስዕል ግራፎች

### ትግበራ 7.1

በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች በሁለት ቡድን በመክለል ከዚህ በታች የተሰጠውን ዳታ በመሰብሰብ ታሊ እና ቁጥርን በመጠቀም በሠንጠረዥ ውስጥዘ አሳዩ፡፡

ቡድን 1፤ ከአፋን ኦሮሞ፣ አማርኛ፣ እንግልዘኛ እና ከሂሳብ ትምህርቶች ውስጥ የትኛውን የበለጠ ትወዱታላችሁ ብላችሁ ቡድን ሁለትን ጠይቁ፡፡

ቡድን 2፤ ከግር ኳስ፣ መረብ ኳስ እና ከሩጫ የትኛውን የበለጠ ትወዱታላችሁ ብላችሁ ቡድን አንድን ጠይቁ፡፡

**አስተዉል/ይ**

በስዕል የቀረቡት ግራፎች ዳታን በቀላሉ ለመግለጽ ይረዳሉ፡፡

### ምሳሌ 1

በቀረበዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የተሰጡትን ዳታዎች በማየት ቀጥለዉ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

| የተማርዎች ስም | መጽሐፍት |
|---|---|
| ቢፍቱ |  |
| ጫላ |  |
| ገመዳ |  |
| ዱሬት |  |
| ኩሜ |  |
| ሐለኬ |  |

ሀ. ቢፍቱ ስንት መጽሐፎች አላት?

ለ. ሐለኬ ስንት መጽሐፎች አላት?

ሐ. ኩሜ ስንት መጽሐፎች አላት?

መ. ዱሬቲ እና ሐለኬ በአንድ ላይ ስንት መጽሐፎች አሏቸዉ?

ረ. በኩሜ እና በጫላ መካከል ያለዉ የመጽሐፍ ልዩነት ስንት ነዉ?

## መልስ

ሀ. 2 መጽሐፍት ለ. 2 መጽሐፍት ሐ. 4 መጽሐፍት

መ. የዱሬቲ መጽሐፍት ብዛት + የሐለኬ መጽሐፍት ብዛት = 3 + 2 = 5

ስለዚህ, 7 መጽሐፍት በአንድ ላይ አሏቸዉ ማለት ነዉ፡፡

ረ. የኩሜ መጽሐፍት ብዛት − የጫላ መጽሐፍት ብዛት = 4 − 3 = 1

ስለዚህ በ 2 መጽሐፍት ይበልጣል::

## መልመጃ 7.1

1. ከዚህ በታች ያለዉ ሰንጠረዥ ተሊሌ ለደንበኞቿ የሸጠችዉን ብርቱካን መጠን በኪሎግራም ይገልፃል፡፡ በዚህ ሰንጠረዥ ላይ በመመስረት ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ፡፡

| ደንበኞች | በኪ.ግ የተሸጠዉ የብርቱካን መጠን(በታሊ) | በኪ.ግ የተሸጠዉ የብርቱካን መጠን ( በቁጥር) |
|---|---|---|
| ሀ | \|\|\|\| | 4 |
| ለ | ~~\|\|\|\|~~ | 5 |
| ሐ | \|\|\| | 3 |
| መ | \|\| | 2 |
| ረ | ~~\|\|\|\|~~ \|\| | 7 |
| ሰ | \|\|\| | 3 |

ሀ. መጠኑ ትንሽ የሆነ ብርቱካን የገዛዉ ማን ነዉ?

ለ. መጠኑ ትልቅ የሆነ ብርቱካን የገዛዉ ማን ነዉ?



ሐ. 5ኪ.ግ ብርቱካን የገዛዉ ማን ነዉ?

መ. ደንበኛ ሐ እና መ በአንድ ላይ ምን ያህል ብርቱካን ገዙ?

2. ከዚህ በታች የቀረቡትን መረጃ ብዛታቸዉን በታሊ እና በቁጥር በሰንጠረዥ ዉስጥ ግለጽ/ጪ፡፡

| ስም | አትክልትና ፍራፍሬ | ታሊ | ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ቲማቲም |  | | |
| ማንጎ |  | | |
| ብርቱካን |  | | |
| አናናስ |  | | |
| እንጆሪ |  | | |

3. በአንድ ትምህርት ቤት ዉስጥ ከ 1-4ኛ ክፍል ያሉትን የተማሪዎች ብዛት ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ዉስጥ በታሊ የተሰጠዉን በቁጥር ጻፍ/ፊ፡፡

| ክፍል | በታሊ | በቁጥር |
|---|---|---|
| 1ኛ |  | |
| 2ኛ |  | |
| 3ኛ |  | |
| 4ኛ |  | |

## 7.2 የግራፍ ምስሎችን ማንበብ እና መግለፅ

የስዕል ግራፎችን በማየት የተለያዩ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡፡

### ትግበራ 7.2

17 ተማሪዎች ፍላጎታቸዉን ተጠይቀዉ 6ቱ የእግር ኳስ፣5ቱ የመረብ ኳስ፣4ቱ የቅርጫት ኳስ እንዲሁም 2ቱ ደግሞ የቴኒስ ጨዋታ ይወዳሉ፡፡ ይህን መረጃ በቡድን በመሆን ሰንጠረዥ ዉስጥ በታሊ እና በቁጥር ግለፁ፡፡

### ምሳሌ 2

ከዚህ በታች ባለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ የኮከብ ምልክት 3 ዶሮዎችን ይወክላል፡፡

ሀ. ደራሬ ስንት ዶሮዎች አሏት?

ለ. ቦና ስንት ዶሮዎች አሉት?

ሐ.የደሜ፣ የአብዲ፣ የቦና እና የደራሬ ዶሮዎች ድምር ስንት ነዉ?

መ. የቦና እና ደራሬ ዶሮዎች ብዛት ስንት ነዉ?

| ስም | አዉራ ዶሮ |
|---|---|
| ደሜ | ★ ★ ★ |
| አብዲ | ★ ★ |
| ቦና | ★ ★ ★ ★ |
| ደራሬ | ★ |

### መፍትሔ

ሀ. አንድ ኮከብ ምልክት 3 ዶሮዎችን ስለሚወክል ደራሬ 3 ዶሮዎች አሏት፡፡

ለ. አንድ ኮከብ ምልክት 3 ዶሮዎችን ስለሚወክል ቦና 12 ዶሮዎች አሉት፡፡


ይኸዉም 3 + 3 + 3 + 3 = 12.

ሐ. የደሜ እና የአብዲ ዶሮዎች ድምር = 9 + 6 + 12 + 3 = 30

መ. የቦና እና ደራሬ ዶሮዎች ልዩነት = 12 — 3 = 9

## መልመጃ 7.2

1. አንድ የቤተ መጽሐፍ ሰራተኛ በቤተ-መጽሐፍት ዉስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የማጣቀሻ መጽሐፍት የሚያሳይ የምስል ግራፍ እንደሚከተለዉ አዘጋጀ።

| | በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉ የማጣቀሻ መፅሐፍት ብዛት |
|---|---|
| አፋን ኦሮሞ |  |
| እንግልዘኛ |  |
| አካባቢ ሳይንስ |  |
| ሒሳብ |  |
| የባህል ትምህርት |  |

አንዱ  ምልክት 10 መጽሐፍትን ይወክላል።

በዚህ የምስል ግራፍ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።


ሀ. ስንት የእንግሊዘኛ የማጣቀሻ መጽሐፍት በቤተ-መጽሐፍቱ ዉስጥ ይገኛሉ?

ለ. ስንት የሂሳብ የማጣቀሻ መጽሐፍት በቤተ-መጽሐፍቱ ዉስጥ ይገኛሉ?

ሐ.ብዛት ያለዉ የማጣቀሻ መጽሐፍት የትኛዉ ነዉ?

መ.ብዛቱ ትንሽ የሆነ የማጣቀሻ መጽሐፍት የትኛዉ ነዉ?

# ምዕራፍ 8




# የጂኦሜትሪ ምስሎች

## 8.1 ምስሎችን በጎንዮሽ ዙር፤ በማንቀሳቀስ እና ነቁጦችን በማዞር የሚገኙ ውጤቶችን መገንዘብ

### ሀ. የጎንዮሽ ዙር

#### ትግበራ 8.1


መስታወት ከፊት ለፊትህ/ሽ ስታስቀምጥ/ጪ ፊትህ እንዴት ዞሮ ታገኘዋለህ?ተወያዩበት፡፡

**የጎንዮሽ ዙር:** ምስሎችን በመስመር ላይ ማንፀባረቅ ማለት ነዉ፡፡


መስታወት ፊት በምንቆምበት ጊዜ ምስላችን ከመስታወቱ እኩል ርቀት ላይ ሆኖ የሚታየንን እንደምሳሌ መዉሰድ ይቻላል፡፡

**ምሳሌ 1**

በመስታዎት ዉስጥ የሚታየዉን የፊት ምስል ተመልከት፡፡




**ምሳሌ:** ከዚህ በታች ያለዉን ምስል ተመልከቱ፡፡




## መልመጃ 8.1

ከዚህ በታች ላሉት ምስሎች በተሰጠዉ መስመር ላይ የጎንዮሽ ዙር ምስላቸዉን ሳል፡፡




## ለ. ማንቀሳቀስ


## ትግበራ 8.2

ማንቀሳቀስ ማለት ምን ማለት ነዉ? የምታዉቀዉን ከጓደኛህ/ሽ ጋር ተወያዩበት ::

**ማንቀሳቀስ**:- አንድን ምስል በተወሰነ ርቀት ከቦታዉ መንሸራተት ማለት ነዉ፡፡

## ምሳሌ 3


ከዚህ በታች ያለዉን ምስል ተመልከት/ቺ፡፡



ማንቀሳቀስ


## ምሳሌ 4

ከዚህ በታች ያለዉን ምስል ብንመለከት ከነበረበት ቦታ በተወሰነ ርቀት ወደፊት መጠጋቱን እናያለን፡፡




## መልመጃ 8.2

ቀጥሎ የቀረቡትን ምስሎች በተሰጠዉ መስመር ላይ በማንቀሳቀስ የሚገኘዉን ምስል ሳል/ይ፡፡




## ሐ. ማዞር


## ትግበራ 8.3

ስዕሎችን ማዞር ማለት ምን ማለት ነዉ? ከጓደኛህ/ሽ ጋር ተወያይ/ዩ፡፡

**ማዞር** : ምስሎችን በተወሰነ እምብርት ላይ ማሽከርከር ማለት ነዉ፡፡


## ምሳሌ 5

በግራ በኩል ያለዉን ምስል ቀስቱ ወደሚያሳየዉ አንድ ጊዜ ብታዞር/ሪ በቀኝ በኩል ያለዉን ምስል ታገኛለህ/ሽ፡፡





## ምሳሌ 6


ከዚህ በታች የቀረቡት ምስሎች በግራ በኩል ያሉትን ወደ ቀኝ አንዴ በማዞር የተገኙ ናቸዉ፡፡



## መልመጃ 8.3


1. ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች በተሰጡት ምልክቶች ላይ በማዞር ሊገኝ የሚችሉትን ምስሎች በቀኝ በኩል ባለዉ ባዶ ቦታ ላይ ሳል/ይ፡፡.

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ.  | | ሐ.  | |


| | | | |
|---|---|---|---|
| ለ.  | | መ.  | |


2. ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች በተሰጠዉ መስመር ላይ በማዞር ሊገኝ የሚችለዉን ምስል ሳሉ፡፡

ሀ.




ለ .





ሐ.



መ.

## 8.2 ሲሜትሪክ እና ሲሜትሪክ ያልሆኑ ቅርፆች

### ትግበራ 8.4

1.አንድ የሬክታንግል ቅርፅ ያለዉ ወረቀት በእኩል ቦታ ብታጠፍ  የሚፈጠረዉ መስመር ምን ይባላል?

2. ሲሜትሪክ ያልሆነ ቅርፅ ምን ይባላል?


**ትርጓሜ**

**የሲሜትሪክ ቅርፅ** አንድ ምስል በመስመር ላይ ታጥፎ በሁለቱም  በኩል ያሉት ነጥቦች ሙሉ በሙሉ  የሚደራረቡ ከሆነ ነዉ፡፡ ምስሉ የታጠፈበት መስመር ደግሞ የሲሜትሪ መስመር ይባላል፡፡


**ሲሜትሪክ ያልሆነ ቅርፅ** ሲሜትሪክ ያልሆነ ቅርፅ ማለት  አንድ ምስል በመስመር ላይ ታጥፎ በሁለቱም  በኩል ያሉት ነጥቦች ሙሉ በሙሉዉ ገጥመዉ የማይደራረቡ ማለት ነዉ፡፡

## ምሳሌ 7

ከዚህ በታች የተሰጡት ምስሎች ሲሜትሪክ እና ሲሜትርክ ያልሆኑ ምስሎች ናቸዉ።.




የሲሜትሪክ ቅርፅ




ሲሜትሪክ ያልሆነ ቅርፅ

## ምሳሌ 8

.ሲሜትሪክ እና ሲሜትሪክ ያልሆኑ ምስሎች።



ሲሜትሪክ ምስሎች




ሲሜትሪክ ያልሆኑ ምስሎች

**አስተዉል/ይ**

አንድ ምስል አንድና ከዚያ በላይ ሲሚትሪክ መስመር ሊኖሩት ይችላል።


## ምሳሌ 9

ከህ በታች ያሉት ምስሎች አንድ እና ከዚያ በላይ የሲሜትሪክ መስመር ያላቸዉ ናቸዉ።




**መልመጃ 8.4**


1.ከቀረቡት ቀርፆች ሲሜትሪክ እና ሲሜትሪክ ያልሆኑትን ለይ/ዪ፡፡




2. ከዚህ በታች የተሰጡት ቅርፆች የሚኖራቸዉን የሰሜትሪክ መስመር ብዛት ፃፍ/ፊ፡፡




3. ከዚህ በታች ያተሰጡት ቅርፆች ሊኖራቸዉ የሚችለዉን የሲሜትሪክ መስመር በሙሉ በማስመር አሳይ/ዪ፡፡








## 8.3 የተለያዩ የጂኦሜትሪ ምስሎች ስያሜ እና ባላቸዉ የጎን ብዛት መለየት

መደበኛ የጂኦሜትሪ ምስሎች ጠለል የጂኦሜትሪ ምስሎች እና ጠጣር የጂኦሜትሪ ምስሎችበመባል ይታወቃሉ፡፡

## 8.3.1 ባለ ብዙ ጎን የጠለል ጂኦሜትሪ ስሞች

### ትግበራ 8.5

ከዚህ በታች ለተሰጡት ምስሎች የጎኖቻቸዉን ብዛት ከስር ፃፍ/ፊ፡፡

|  |  |  |  |
|---|---|---|---|
| | | | |

**ጎነ-ብዙ፡** ጎኑ ቀጥታ መስመር የሆነ እና የተለያየ የጎን ብዛት ያለዉ ጠለል ምስል ነዉ፡፡

### ምሳሌ 10

የጎነ-ብዙ ስም እና የጎኖቻችዉ ብዛት

| የጎነ-ብዙ ስም | የጎኖች ብዛት |
|---|---|
| ጎነ-ሦስት | 3 |
| ጎነ-አራት | 4 |
| ጎነ-አምስት | 5 |
| ጎነ-ስድሰት | 6 |
| ጎነ-ሰባት | 7 |
| ጎነ-ስምንት | 8 |
| ጎነ-ዘጠኝ | 9 |
| ጎነ-አስር | 10 |


**አስተዉል.**

ጎነ ብዙ ጠለል የተሰራበት ቀጥታ መስመር **ጎን** ይባላል፡፡

ሁለት ጎኖች የሚገናኙበት ቦታ ዘዌ ይባላል፡፡






## ምሳሌ 11

ከዚህ በታች ያለዉን ጎነ ብዙ ተመልከት/ቺ፡፡




## መልመጃ 8.5





ከዚህ በታች ላሉትን ምስሎች ስሞቻቸዉንና የጎኖቻቸዉን ብዛት በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡


| | |
|---|---|
|  | የጎነ-ብዙ ስም ______ የጎን ብዛት ______ |
|  | የጎነ-ብዙ ስም ______ የጎን ብዛት ______ |
|  | የጎነ-ብዙ ስም ______ የጎን ብዛት ______ |
|  | የጎነ-ብዙ ስም ______ የጎን ብዛት ______ |
|  | የጎነ-ብዙ ስም ______ የጎን ብዛት ______ |

## 8.3.2 ጠጣር ጂኦሜትሪ

### ትግበራ 8.6


1. ከተሰጡት የጂኦምትሪ ምስሎች ጠጣር ጂኦሜትሪ የሆኑትን ለይ/ዩ፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ.  ሠ. 

ረ.  ሰ.  ሸ.  ቀ. 

## ምሳሌ 12


ከዚህ በታች የሚታዩት ጠጣር ጂኦሜትሪ ምስሎች ናቸዉ።





## የጠጣር ጂኦምትሪ ምስል ገጽ እና ነቁጥ

አብዛኛዎቹ የጠጣር ጂኦምትሪ ምስሎች ገጽ እና ነቁጥ አላቸዉ። ነገር ግን ነቁጥ የሌላቸዉ አሉ።

## ምሳሌ 13




## ምሳሌ 14





የጠጣር ምስሎች ነቁጦች እና ገጾች

**አስታዉል/ይ**







እስፌር እና ሲሊንደር ገጽ ሲኖራቸዉ ነቁጥ የላቸዉም።

## ምሳሌ 15




## መልመጃ 8.6

ከዚህ በታች ላሉት ምስሎች የገፅ እና ነቁጥ ብዛት በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |
| ገጽ ______<br>ነቁጥ____ | ገጽ ______<br>ነቁጥ____ | ገጽ ______<br>ነቁጥ____ | ገጽ ______<br>ነቁጥ____ | ገጽ ______<br>ነቁጥ____ | ገጽ ___<br>ነቁጥ___ |

# 8.4 የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት በመገንዘብ መጥቀስ




## የጎነ ሦስት እና ጎነ አራት ምስል ባህሪያት

### ትግበራ 8.7

1. ጎነ ሦስቶች ያላቸዉን ባህሪያት በቡድን በመወያየት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡.
2. በምትማሩትበት ክፍል ዉስጥ ጎነ-አራት ያላቸዉን ነገሮች ለመምህርህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡





**ጎነ-ሦስት፤** ሦስት ጎኖች እና ሦስት ዘዌ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ ጎኖችን መሰረት በማድርግ በሦስት ይከፈላሉ፡፡እነሱም፤

1. እስኬለን ጎነ-ሦስት
2. ሁለት ጎኑ እኩል ጎነ-ሦስት
3. ጎነ እኩል ጎነ-ሦስት

| እስከለን ጎነ-ሦስት | ሁለት ጎኑ እኩል ጎነ-ሦስት | ጎነ እኩል ጎነ-ሦስት |
|---|---|---|
|  |  |  |
| ሦስቱም ጎኖች እኩል ያልሆኑ ሦስቱም ዘዌዎች እኩል ያልሆኑ | ሁለቱ ጎኖች ብቻ እኩል የሆኑ<br>ሁለቱ ዘዌዎች ብቻ እኩል የሆኑ | ሦስቱም ጎኖች እኩል ያሆኑ ሦስቱም ዘዌዎች እኩል ያሆኑ |


. ጎነ-አራት አራት ጎኖችና አራት ነቁጦች አለዉ። ያተለያዩ ዓይነት ጎነ-አራቶች አሉ። እነሱም

1. ሬክታንግል
2. ካሬ
3. ፓራለሎግራም
4. ሮምቦስ እና ትራፒዝየም ናቸዉ።.


| ጎነ-አራቶች | ባህሪያት | የምስሎች ቅርፅ |
|---|---|---|
| ፓራለሎግራም | ተዛማጅ ጎኖች እኩል ናቸው |  |
| ሬክታንግል | ተዛማጅ ጎኖች እኩል ናቸው<br>አራቱም ዘዌዎች እኩል ናቸው |  |
| ካሬ | አራቱም ጎኖች እኩል ናቸው<br>አራቱም ዘዌዎች እኩል ናቸው |  |
| ሮምቦስ | አራቱም ጎኖች እኩል ናቸው |  |


## መልመጃ 8.7

1. ከዚህ በታች ለተሰጡት ምስሎች የዘዌያቸዉን ብዛት ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ.  ____________

ለ.  ____________

ሐ.  ____________

መ.  ____________

2. ሦስቱን የጎነ-ሶስት ዓነቶች ፃፍ/ፊ፡፡

3. የጎን አራት አይነቶችን ፃፍ/ፊ፡፡

# ምዕራፍ 9



# የርዝመት መጠነ ቁስ እና ይዘት መስፈሪያዎች ዩኒቶች

## 9.1 ርዝመትን በሚሊ ሜትር፣ሴንቲ ሜትር፣በሜትር እና በኪሎ ሜትር መስፈር

### ሀ. ሚሊ ሜትር(ሚ.ሜ) እና ሴንቲ ሜትር (ሴ.ሜ)

### ትግበራ 9.1

1. ከአምስቱ የእጅ ጣቶቻችን መካከል አጭሩ የትኛው ነው?
2. ማስመሪያ በመጠቀም የተሰጡትን ውስን ቀጥታ መስመሮች ርዝመት በሴንቲ ሜትር እና በሜትር በመጽሐፍህ/ሽ ላይ ስፈር/ሪ።

    ሀ. ———

    ለ. ————————————————

    ሐ. ——————————

**አስታውስ/ሽ**

ሴንቲ ሜትር እና ሜትር የርዝመት መስፈሪያ ዩኒቶች ናቸው።

ሴንቲ ሜትር እና ሜትር አጫጭር ርዝመቶችን ለመስፈር ይጠቅማሉ።

### ምሳሌ 1


ሀ. የተሰጠው የእርሳስ ርዝመት ስንት ነው?



**መልስ**

በምስሉ ላይ የተሰጠው እርሳስ ርዝመት 16 ሴ.ሜ ነው፡፡

ለ. የባትሪ ድንጋይ ርዝመት ስንት ነው?




☐ ሚ.ሜ

**መልስ**

በምስሉ ላይ የተሰጠው እርሳስ ርዝመት 30 ሚ.ሜ ነው፡፡

የሴንቲ ሜትር እና ሚሊ ሜትር ተዛምዶ

1 ሴንቲ ሜትር = 10 ሚሊ ሜትር

1 ሴ.ሜ = 10 ሚ.ሜ

## መልመጃ 9.1

1. ከሴንቲ ሜትር እና ሚሊ ሜትር የሚመችን መስፈሪያ በመጠቀም ከዚህ በታች የተሰጡትን ነገሮች ርዝመት ስፈር/ሪ፡፡
   ሀ. የሂሳብ መጽሐፋችን ርዝመት
   ለ. የክፍላቹን በር እና መስኮት ርዝመት
   ሐ. በክፍላችሁ ውስጥ ያለውን የጠረጴዛ ርዝመት
2. ከሴንቲ ሜትር እና ሚሊ ሜትር ውስጥ የሚመችን መስፈሪያ በመጠቀም ከዚህ በታች የተሰጡትን ነገሮች ርዝመት ስፈር/ሪ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. |   | ሐ  | ሠ  |
| ለ. |  | መ  | ረ  |

## ለ. ሜትር እና ኪሎ ሜትር

### ትግበራ 9.2

ከዚህ በታች የተሰጡትን ለመስፈር ከሜትር እና ኪሎ ሜትር አመቺ የሆነዉ የትኛው ነው? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኃላ የጥያቄዎቹን መልስ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ቁመታችሁ

ለ. ከመኖሪያ ቤታችሁ እስከ ትምህርት ቤታችሁ ያለውን ርቀት

ሐ. ከፊንፊኔ እስከ አዳማ ያለው ርቀት

መ. ከመማሪያ ክፍላችሁ እስከ ስፖርት ሜዳችሁ ያለው ርቀት

ሠ. የአባይ ወንዝ ርዝመት

ረ. የእንጦጦ ተራራ ከፍታ

**ማስታወስ/ሽ**

1. ሜትር እና ኪሎ ሜትር ረጃጅም ርቀቶችን ለመስፈር ያገለግላሉ፡፡
2. የሜትር እና ኪሎ ሜትር ተዛምዶ

1 ሜትር = 100 ሴንቲ ሜትር


1 ኪሎ ሜትር = 1000 ሜትር

1ሜ = 100 ሴ.ሜ እና

1 ኪ.ሜ = 1000 ሜ

### መልመጃ 9.2

1. ከተሰጡት የርዝመት መስፈሪያዎች ውስጥ የተሰጡትን የምስሎች ርዝመት ለመስፈር የሚጠጋዉን ምረጥ/ጪ፡፡

| ሀ. | ለ. | ሐ. |
|---|---|---|
|  |  |  |
| የቤት በር<br>ሀ. 2ሴ.ሜ<br>ለ. 2 ሜ<br>ሐ. 2ኪ.ሜ | ከፊንፊኔ እስከ ሆሎታ ያለው ርቀት<br>ሀ. 25ሴ.ሜ<br>ለ. 25ሜ<br>ሐ. 25ኪ.ሜ | የልጁ ቁመት<br>ሀ. 50ሴ.ሜ<br>ለ. 50ሜ<br>ሐ. 50ኪ.ሜ |

2. የተጠሰውን ባዶ ቦታ ሙላ/ይ

| | |
|---|---|
| ሀ. 100 ሚ.ሜ = ______ ሴ.ሜ | ሠ. 6000ሜ = ___ኪ.ሜ |
| ለ. 3 ኪ.ሜ = ________ ሜ | ረ. 7 ሜ = ________ሴ.ሜ |
| ሐ. 900 ሴ.ሜ = _______ ሜ | ሰ. 5ሜ = _______ሚ.ሜ |
| መ. 4000 ሚ.ሜ = _____ሴ.ሜ | ሸ. 800 ሚ.ሜ = __ሴ.ሜ |

## 9.2 ተመሳሳይ የርዝመት ዩኒቶች ያላቸውን መስፈሪያዎች መደመር እና መቀነስ

### ትግበራ 9.3

በሲንቦ መኖሪያ ቤት እና ትምህርት ቤት መካከል ያለው ርቀት 150 ሜ ቢሆን ትምህርት ቤት ደርሳ ለመመለስ ስንት ሜትር ትጓዛለች?

### ምሳሌ 2

የ3 ሜትር እና 50 ሜትር ድምር ስንት ነው?

**መፍትሄ**

3 ሜትር + 50 ሜትር = 53 ሜትር ይሆናል።

**ምሳሌ 3**

የ1 ኪ.ሜ እና 7 ኪ.ሜ ድምር ስንት ነው?

**መፍትሄ**

1 ኪ.ሜ + 7 ኪ.ሜ = 8 ኪ.ሜ ይሆናል።

**ምሳሌ 4**

12 ሜትር ከሚረዝመው ሽቦ 5 ሜትር ሽቦ ቢቆረጥ ስንት ሜትር ሽቦ ይቀራል?

**መፍትሄ**

ከረጅሙ ሽቦ ላይ አጭሩን በመቀነስ ይገኛል።

ይኸውም 12ሜ — 5ሜ = 7ሜ

ስለዚህ 7ሜ ሽቦ ይቀራል።

## መልመጃ 9.3

1. የሚከተሉትን አስላ/ይ።


ሀ . 60 ሴ.ሜ + 100ሴ.ሜ = ______ ለ . 56ሴ.ሜ + 44 ሴ.ሜ =______

ሐ . 32 ኪ.ሜ − 30ኪ.ሜ = ______ መ . 92ሴ.ሜ − 24 ሴ.ሜ =______

ሠ. 324ሜ + 656ሜ = __________ ረ. 830ሜ − 460ሜ = ________

2. ገመቹ 40 ኪ.ሜ ርቀት ያለውን መንገድ ለመሄድ ፈለገ። በመኪና 35 ኪ.ሜ ተጉዞ የቀረውን በእግር ቢጓዝ በእግር የተጓዘውን ርቀት ፈልግ/ጊ

# 9.3 መጠነ ቁስን በሚሊ ግራም ፣ በግራም፣ በኪሎ ግራም እና በኩንታል መስፈር



## ሀ. ሚሊግራም እና ግራም

### ትግበራ 9.4

1. የሚታውቃቸውን /ቂያቸውን የመጠነ ቁስ መስፈሪዎች ለጓደኞችህ/ሽ ተናገር/ሪ፡፡
2. የሰው መጠነ ቁስ በምን ይመዘናል?
3. ከዚህ በታች የተሰጡት የነገሮች መጠነ ቁስ ለመመዘን ሚሊ ግራም፣ ግራም፣ ኪሎ ግራም እና ኩንታል ውስጥ ምቹ የሆነውን ተናገር/ሪ፡፡
   ሀ. የአልባሳት ቁልፍ መጠነ ቁስ
   ለ. የአንድ እርሳስ መጠነ ቁስ
   ሐ. የአንድ ሰንጋ መጠነ ቁስ
   መ. የሂሳብ መጽሐፋችሁን መጠነ ቁስ
   ሠ. አንድ መኪና መሸከም የሚችለውን የስኳር መጠን

**አስታውስ/ሽ**

ሚሊ ግራም (ሚ.ግ) እና ግራም(ግ) የመጠነ ቁስ መለኪያዎች ናቸው ፡፡

ሚሊ ግራም(ሚ.ግ) መጠነ ቁሳቸው በጣም ቀላል የሆኑ ነገሮችን ለመመዘን ይረዳል፡፡

1 ግራም = 1000 ሚሊ ግራም

1ግ = 1000 ሚ.ግ

ግራም(ግ) መጠነ ቁሳቸው ቀላል የሆኑ ነገሮችን ለመመዘን ይረዳል፡፡

**ምሳሌ 5**

5 ግ = _____ ሚ.ግ ?

**መፍትሄ**

1 ግ = 1000 ሚ.ግ ስለሆነ በ5 በ 1000 ማባዛት ነው::

ይኸውም 5 × 1000ሚ.ግ = 5000ሚ.ግ ይሆናል።

ስለዚህ 5 ግ ውስጥ 5000 ሚ.ግ አለ።

## ለ. ኪሎ ግራም (ኪ.ግ) እና ኩንታል(ኩ)

ኪሎ ግራም እና ኩንታል የመጠነ ቁስ ዩኒቶች ናቸው።



ይህ ሙዝ 1 ኪ.ግ ነው




1 ኩንታል ስኳር

## የኪሎ ግራም እና ኩንታል ተዛምዶ

ኪሎ ግራም እና ኩንታል መጠነ ቁሳቸው ትልቅ የሆኑትን ለመመዘን ይጠቅማሉ።

1 ኪሎ ግራም = 1000 ግራም

1 ኩንታል = 100 ኪሎ ግራም

**ምሳሌ 6**

3 ኩንታል = _____ ኪሎ ግራም?

**መፍትሄ**

1ኩንታል = 100 ኪሎ ግራም ስለሆነ 3 በ 100ኪሎ ግራም ማባዛት ነው፡፡

ይኸውም 3 × 100 ኪሎ ግራም = 300 ኪሎ ግራም ይሆናል፡፡

ስለዚህ 3 ኩንታል ውስጥ 300 ኪሎ ግራም አለ ማለት ነው፡፡

## መልመጃ 9.4

መጠነ ቁሳቸውን ለመስፈር የሚመቸውን የመስፈሪያ ዩኒቶችን ምረጥ/ጪ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. |  | ሀ. 3ኪ.ግ   ለ.3ግ   ሐ.3 ሚ.ግ |
| 2. |  | ሀ. 2ኪ.ግ   ለ.2ግ   ሐ. 2ሚ.ግ |
| 3. |  | ሀ. 3ኪ.ግ   ለ.3ግ   ሐ. 3ሚ.ግ |
| 4. |  | ሀ. 700ኪ.ግ   ለ.700ግ   ሐ.700 ሚ.ግ |
| 5. |  | ሀ. 10ኪ.ግ   ለ.10ግ   ሐ. 10ሚ.ግ |

6. ባዶ ቦታ ሙላ/ይ፡፡

ሀ. 1ግ = ________ ሚ.ግ    ሠ. 7 ግ = __________ሚ.ግ

ለ. 1ኪ.ግ = _______ግ    ሰ. 5000 ሚ.ግ = ___ግ

ሐ. 1 ኩንታል = __ኪ.ግ    ረ. 6 ኩንታል = _____ ኪ.ግ

መ. 10,000ግ = ___ ኪ.ግ    ሸ. 800 ኪ.ግ = _______ ኩንታል

## 9.4 ተመሳሳይ የመጠነ ቁስ መስፈሪያ ዩኒት ያላቸውን መደመር እና መቀነስ

### ትግበራ 9.5

ከዚህ በታች የተሰጡትን አስላ/ይ፡፡


ሀ. 85ግ + 53ግ = _______ግ    ለ. 90ኪ.ግ + 110ኪ.ግ = ___ኪ.ግ


ሐ. 4000 ኪ.ግ + 60ኪ.ግ = ___ ኪ.ግ    መ. 900ግ − 200ግ =_________ግ

ሠ. 2000ግ + 2ግ = _____ግ    ረ. 100ሚ.ግ − 20ሚ.ግ = __ሚ.ግ

### ምሳሌ 7

የፍየል እና የበግ መጠነ ቁስ አንድ ላይ ስንት ይሆናል?




### መፍትሄ

የፍየል መጠነ ቁስ 40 ኪ.ግ እና የበግ መጠነ ቁስ 50 ኪ.ግ ነው፡፡

የሁለቱን መጠነ ቁስ አንድ ላይ ስንደምራቸው 40 ኪ.ግ + 50 ኪ.ግ = 90 ኪ.ግ ይሆናል፡፡

ስለዚህ የፍየል መጠነ ቁስ እና የበግ መጠነ ቁስ አንድ ላይ 90ኪ.ግ ይሆናል፡፡

### መልመጃ 9.5

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን አስላ/ይ፡፡

   ሀ. 800ግ + 500ግ = _____ግ ለ. 6 ኩን + 400ኩን=_______ኩን

   ሐ. 500ሚ.ግ − 300ሚ.ግ = ____ሚ.ግ መ. 100 ኪ.ግ − 88ኪ.ግ = __ኪ.ግ

2. ወ/ሮ አንጋቱ ሱቅ ሄዳ 6ኪ.ግ ስኳር፣ 5ኪ.ግ ሩዝ እና 30ኪ.ግ የስንዴ ዱቄ ገዙ፡፡

   ሀ. አንድ ላይ ምን ያህል ስኳር እና ሩዝ ገዙ?

   ለ. አንድ ላይ ምን ያህል ስኳር እና የስንዴ ዱቄት ገዙ?

   ሐ. አንድ ላይ ምን ያህል ስኳር፣ሩዝ እና የስንዴ ዱቄት ገዙ?

3. ደንበሊ ከገዛው 675 ኪ.ግ ብርቱካን ውስጥ 395 ኪ.ግ መልሰው ቢሸጥ ምን ያህል ብርቱካን ይቀሩታል?

## 9.5 የይዘት መስፈሪያ ዩኒቶች ሚሊ ሊትር እና ሊትር

### ትግበራ 9.6

ከዚህ በታች የተሰጡትን ምስሎች ለመስፈር ከሚሊ ሊትር እና ሊትር ትኛዉ ትጠቀማለህ/ሽ?

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. |  | 2. |  | 3. |  |
| 4. |  | 5. |  | 6. |  |

## ማስታወሻ

ሚሊ ሊትር (ሚ.ሊ) እና ሊትር(ሊ) የፈሳሽ መስፈሪያ ዩኒቶች ናቸው፡፡

ሚሊ ሊትር (ሚ.ሊ) በጣም ጥቂት ይዘቶችን ለመስፈር ያገለግላል፡፡


ሊትር ጥቂት ይዘቶችን ለመስፈር ያገለግላል፡፡

1ሊትር = 1000 ሚሊ ሊትር

1ሊ = 1000 ሚ. ሊ

## መልመጃ 9.6

ትክክል የሆነውን የይዘት መስፈሪያ ዩኒትን ምረጥ/ጪ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. |  | 2. |  | 3. |  |
| | ሀ. 25ሊ<br>ለ. 25ሚ.ሊ | | ሀ. 250ሊ<br>ለ.250ሚ.ሊ | | ሀ. 2ሊ<br>ለ.2ሚ.ሊ |
| 4. |  | 5. |  | 6. |  |
| | ሀ. 150ሊ<br>ለ.150ሚ.ሊ | | ሀ. 1ሊ<br>ለ. 1ሚ.ሊ | | ሀ. 1ሚ.ሊ<br>ለ. 1ሊ |

ባዶ ቦታ ሙላ/ይ፡፡

**7.** 5 ሊ = __________ ሚ.ሊ

**8.** 500 0ሚ.ሊ = _______ ሊ

**9.** 1000ሚ.ሊ = _________ ሊ

**10.** 9 ሊ = _______ሚ.ሊ

## 9.6 ተመሳሳይ የይዘት መስፈሪያ ዩኒቶች ያላቸውን መደመር እና መቀነስ

### ምሳሌ 8

ሲምቦ የወተት ላም አላት፡፡ በቀን ሁለት ጊዜ ወተት ትሸጣለች፡፡ ጧት 13 ሊትር እንዲሁም ማታ 15 ሊትር ብትሸጥ በአጠቃላይ በቀን ምን ያህል ሊትር ወተት ትሸጣለች?

### መፍትሄ

ሲምቦ በቀን ምን ያህል ሊትር ወተት እንደምትሸጥ ለማወቅ ጧት እና ማታ የሚታገኛውን አንድ ላይ መደመር ነው፡፡

ይኸውም 13 ሊትር + 15 ሊትር = 28 ሊትር ይሆናል፡፡

ስለዚህ ጠዋት እና ማታ አንድ ላይ 28 ሊትር ትሸጣለች፡፡

### መልመጃ 9.7

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን አስላ/ይ፡፡
   ሀ. 20ሊ.+ 25ሊ. = _  ለ. 30ሚ.ሊ.− 15ሚ.ሊ. =__
   ሐ. 80ሚ.ሊ. + 30ሚ.ሊ. = ___  መ. 90ሊ.− 10ሊ. = __
2. 900 ሚ.ሊ. የጀግ ዉኃ ላይ 250 ሚ.ሊ. ቢጨመርበት ስንት ሚ.ሊ. ይሆናል?
3. አያንቱ ከገዛችዉ 25ሊ. የምግብ ዘይት ላይ 9 ሊትር ለእናቷ ብትቀንስላቸው ስንት ሊትር ዘይት ይቀርላታል?
4. ጫልቱ ከላት 478 ሊ. ነዳጅ ላይ 239 ሊትር ብትጠቀምበት ስንት ሊትር ነዳጅ ይቀርላታል?
5. ወ/ሮ ቦንቱ ለ3 ሰዎች ወተት ኮንትራት ሰጠች፡፡ ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ሎሚ 3 ሊትር፣ፊይኔ 2 ሊትር እንደሁም ቀጄላ 4 ሊትር የሚወስዱ ከሆነ
   ሀ. የበለጠ ወተት የምወስደው ማነው?
   ለ. ጥቂት ወተት የምወስደው ማነው?
   ሐ. የበለጠ ወተት የምወስደው ጥቂት ወተት ከምወስደው በምን ያህል ይበልጣል?

## 9.7 ከርዝመት፣መጠነ ቁስ እና ይዘት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የቃላት ፕሮብሌሞች

### ምሳሌ 9

አብዲ 2 ኪሎ ሜትር ሮጠ፡፡ አዱኛ 500 ሜትር ቢሮጥ በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው ርቀት ምን ያህል ነው?

### መፍትሄ

አብዲ እና አዱኛ የሮጡትን ርቀት በመቀነስ እናገኛለን፡፡

ይኸውም 2 ኪሎ ሜትር = 2000 ሜትር ስለሆነ

2000 ሜትር — 500ሜትር = 1500 ሜትር ይሆናል፡፡

ስለዚህ ልዩነቱ 1500 ሜትር ይሆናል፡፡

### መልመጃ 9.8

1. የሮባ ቦርሳ 5ኪሎ ግራም ከ75 ግራም ይከብዳል፡፡ የአነኔ ቦርሳ ደግሞ 7 ኪሎ ግራም ከ 20 ግራም ይከብዳል፡፡ የማን ቦርሳ የበለጠ ይከብዳል?
2. አንድ በርሜል 1000 ሊትር ውኃ ይይዛል፡፡ በውስጡ 450 ሊትር ውኃ ቢኖረው ለመሙላት ስንት ሊትር ውኃ ይጎለዋል?
3. ጫላ ሳይክሉን በቀን 8 ኪሎ ሜትር ይነዳል፡፡ በቀን ስንት ሜትር ይነዳል?
4. ኦብሴ በሁለት ቀናት 15 ሊትር ውኃ ትጠቀማለች፡፡ በቀሩት የሳምንቱ ቀናት ውስጥ ደግሞ 27 ሊትር ትጠቀማለች፡፡ በሳምንት ውስጥ ምን ያህል ሊትር ውኃ ትጠቀማለች?
5. የሁለት ህፃናት ቁመት 44 ሴንቲ ሜትር እና 35 ሴንቲ ሜትር ነው፡፡ በሁለት ህፃናት ቁመት መካከል ያለው ልዩነት ስንት ሴንቲ ሜትር ነዉ?

ምዕራፍ

10



# የኢትዮጵያ ገንዘብ ምንዛሬ

## 10.1 የምንዛሬ ዩኒቶችን መቀየር

### 10.1.1 የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና የሣንቲም ዲናሮች ተዛምዶ

#### ትግበራ 10.1

በኢትዮጵያ ገንዘብ ኖቶችና ዲናሮች ያላቸዉን ዝምድናና ግንኙነታቸዉን አብራሩ፡፡

የሚከተሉትን ተዛምዶ አስተዉል!

100 ሣንቲሞች = 1 ብር

100 ብሮች = 1 ባለ መቶ ብር



ዲናሮች



ኖቶች

## 10.1.2 የኢትዮጵያ ገንዘብ ዲናሮች እና ኖቶች ስዕል

### ሀ. የኢትዮጵያ ገንዘብ የሣንቲም ዲናሮች ስዕል



ባለ 1 ሣንቲም



ባለ 5 ሣንቲም



ባለ 10 ሣንቲም



ባለ 25 ሣንቲም



ባለ 50 ሣንቲም



ባለ 1 ብር

**ምሳሌ 1**

በባለ አንድ ብር ዲናር እና በሳንቲሞች መካከል ያላዉን ተዛምዶ የሚያሳየዉን ምስል ተመልከቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የባለ 1 ብር ዲናር ምስል  |  |  |  |  |
| | ስንት ባለ 5 ሣንቲሞች አሉት? | ስንት ባለ 10 ሣንቲሞች አሉት? | ስንት ባለ 25 ሣንቲሞች አሉት? | ስንት ባለ 50 ሣንቲሞች አሉት? |
| **መፍትሔ** | 20 አለዉ፡፡. | 10 አለዉ፡፡ | 4 አለዉ፡፡ | 2 አለዉ፡፡ |

### ለ. የኢትዮጵያ ገንዘብ የብር ኖቶች ምስል




ባለ 5 የብር ኖት



ባለ 10 የብር ኖት



ባለ 50 የብር ኖት



ባለ 50 የብር ኖት



ባለ 200 የብር ኖት

## ምሳሌ 2


አንድ ባለ 200ብር ኖት ከሌሎች የብር ኖቶች ጋር ያለዉን ዝምድና የሚያሳየዉን ምስል ተመልከቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  **የባለ 200 ብር ኖት ምስል** |  |  |  |  |
| | ስንት ባለ 5 የብር ኖቶች አሉት? | ስንት ባለ 10 የብር ኖቶች አሉት? | ስንት ባለ 50 የብር ኖቶች አሉት? | ስንት ባለ 100 የብር ኖቶች አሉት? |
| **መፍትሔ** | 40 አለዉ፡፡. | 20 አለዉ፡፡. | 4 አለዉ፡፡ | 2 አለዉ፡፡ |

## መልመጃ 10.1

1.ከዚህ በታች በተሰጡት የብር ኖት ምስሎች ላይ በመመርኮዝ ጥያቄዎቹን መልስ/ሽ፡፡

ሀ.



አንድ ባለ 100 ብር ኖት ስንት ባለ 50 ብር ኖቶች ይሆናል?

ለ.



አንድ ባለ 50 የብር ኖት ስንት ባለ 10 ብር ኖቶች ይሆናል?

ሐ.



አንድ ባለ 5 የብር ኖት ስንት ባለ 1 ብር ዲናር ይሆናል?

መ.



ባለ 1 ብር ዲናር ስንት ባለ 1 ሣንቲም ዲናሮች ይሆናል?

2. ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ በሆነ መልስ ሙላ/ይ፡፡

ሀ. 1 ባለ መቶ ብር ኖት _______________ ባለ አምስት ብር ኖት ይሆናል፡፡

ለ. 3 ባለ ሃምሳ ብር ኖት _______________ ባለ አስር ብር ኖት ይሆናል፡፡

ሐ. 1 ባለ አስር ብር ኖት __________ ባለ ሃምሳ ሣንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

መ. 1 ባለ አምስት ብር ኖት_______________ ባለ ሃያ አምስት ሣንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

ሠ. 1 ባለ አምስት ብር ኖት እና 1 ባለ አንድ ዲናር ብር ______ባለ ሃምሳ ሣንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

3. ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ትክክለኛ በሆነ መልስ ሙላ/ይ፡፡

ሀ. 3 ብር________________ባለ 25 ሳንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

ለ. 10 ብር ________________ባለ 50 ሳንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

ሐ. 5 ብር________________ባለ 10 ሳንቲም ዲናር ይሆናል፡፡ .

መ. 2 ብር ዲናር________________ባለ 5 ሳንቲም ዲናር ይሆናል፡፡

## 10.2 ከኢትዮጵያ የገንዘብ ምንዛሬ ጋር ተዛምዶ ያላቸውን የቃላት ፐሮብሌሞች መፍታት

### ምሳሌ 3

ሰንዳቤ አንድ ደብተር በ12 ብር ገዛች፡፡ በ48 ብር ስንት ደብተሮችን ትገዛለች?

**መፍትሔ**

48 ብር ለ 1 ደብተር ዋጋ በማካፈል ታገኛለህ/ሽ::

ይኸውም 48 ÷ 12 = 4 ይሆናል፡፡ ስለዚህ 4 ደብተሮች ትገዛለች ማለት ነዉ፡፡

### ምሳሌ 4

ቢፍቱ አንድ እርሳስ እና ሁለት እስክሪብቶዎችን ገዝታ 30ብር ከፈለች፡፡ ለማገርዉ ስንት ባለ 10 የብር ኖቶች ያስፈልጓታል?

**መፍትሔ**

30 ብር ባለ 10 የብር ኖት 3 ይሆናል፡፡

ስለዚህ 3 ባለ 10ብር የብር ኖት ትከፍላለች ማለት ነዉ፡፡

### ምሳሌ 5

ኡርጌሳ አንድ ባለ100 የብር ኖት በኪሱ ይዟል፡፡ ስንት ባለ 5 የብር ኖቶች ይሆናሉ?

**መፍትሔ**

ይህንን 100ብር ለአምስት በማካፈል ማግኘት ይቻላል፡፡

ይኸዉም 100 ÷ 5 = 20 ነዉ፡፡

ስለዚህ ባለ 5ብር የብር ኖት 20 ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

### ምሳሌ 6

ገነሜ በ20 ብር ከ 75 ሳንቲም የጥፍር ቀለም እና በ3 ባለ 10ብር ኖቶች ሁለት ደብተሮችን ገዛች፡፡ በአጠቃላይ ለጥፍር ቀለምና ደብተሮች ግዢ ያወጣችዉ ስንት ብር እና ሳንቲም ነዉ?

## መፍትሔ


3 ባለ 10ብር ኖቶች ማለት 30ብር ነዉ፡፡

ስለዚህ 20ብር ከ 75 ሳንቲም + 30ብር = 50ብር ከ75 ሳንቲም ይሆናል፡፡

## መልመጃ 10.2

1.በሰንጠረዡ ዉስጥ ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛ በሆነ መልስ ባዶ ቦታ ላይ ሙላ/ይ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.  _____ብር ____ ሳንቲም | ለ.  _____ብር _____ሳንቲም |
| ሐ.   ____ባለ 10ብር እና____ ባለ 1ብር ዲናር ያስፈልጋል፡፡ | መ.   __ባለ 200ብር__ባለ 100ብር__ባለ 10ብር እና__ባለ 25 ሳንቲም ያስፈልጋል |

| ረ. | ሠ. |
|---|---|
|   __ባለ 10ብር እና __ባለ 5ብር |     __ባለ 100ብር__ባለ 50ብር__ባለ 10ብር __ባለ 1ር እና__ባለ 10 ሳንቲም |

2.ከታች ያለዉን ሰንጠረዥ በምሳሌዉ መሰረት 100ሣንቲም ሊሰጡን በሚችሉ ዲናሮች ሙላ/ይ::

| | |  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 5 ዲናሮችን በመተቀም | | 1 | 2 | 1 | 1 |
| 2 | 6 ዲናሮችን በመተቀም | | | | | |
| 3 | 7 ዲናሮችን በመተቀም | | | | | |
| 4 | 10 ዲናሮችን በመተቀም | | | | | |
| 5 | 12 ዲናሮችን በመተቀም | | | | | |
| 6 | 24 ዲናሮችን በመተቀም | | | | | |

3. አንድ ደርዘን ደብተር በ188ብር ይገዛል:: ቶላ አንድ ደርዘን ደብተር ለመግዛት ባለ 200ብር ቢከፍል ስንት ባለ 10 እና ባለ 1ብር ዲናር መልስ ይኖረዋል?

4. የደሜ አባት ጫማ እንድትገዛበት አንድ ባለ 200ብር ኖት ሰጧት:: በ150ብር ብትገዛ ስንት መልስ ይኖራታል?

# ምዕራፍ 11



2፡ 30




# የኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር

## 11.1 ሰዓትን ማንበብ

### ትግበራ 11.1

ከዚህ በታች በተሰጡት የሰዓት ምስልን በመመልከት ስንት ሰዓት እንደሆነ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ.



ለ.




መ.



**አስታውስ/ሽ**

1. ግዜን ለመስፈር ሰዓትን እንጠቀማለን፡፡
2. 1 ሰዓት 60 ደቂቃ ነው፡፡



የደቂቃ ቆጣሪ ጨረር ከ12 ተነስቶ 1ላይ ሲደርስ 5 ደቂቃ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የደቂቃ ቆጣሪ ጨረር እንቅስቃሴ በአምስት አምስት ደቂቃ በመቁጠር ሰዓትን መናገር ይቻላል፡፡

**ምሳሌ 1**

ይህ ምስል 3 ሰዓት ከ 25 ደቂቃ ያሳያል፡፡ ሲጻፍም 3:25 ይሆናል፡፡




**ምሳሌ 2**


ይህ ምስል 8 ሰዓት ያሳያል፡፡ ሲጻፍም 8:00 ይሆናል፡፡



## መልመጃ 11.1

1. የተሰጡትን የሰዓት ምስሎች በማየት ስንት ሰዓት እንደሚያሳይ ተናገር/ሪ፡፡

ሀ







ለ



ሐ



2. የተሰጡትን የሰዓት ስዕሎች በደብተርህ/ሽ ላይ በትክክል በመሳል ትክክለኛውን የሰዓት እና የደቂቃ ጨረር በመጠቀም አሳይ/ዪ፡፡

| ሀ.  | ለ.  | ሐ.  | መ.  |
|---|---|---|---|
| 9.25 | 2.35 | 7.05 | 3.10 |

3. የሰዓት ቆጣሪ ጨረር ከ12 ሰዓት ተነስቶ 1 ላይ ስደርስ ስንት ሰዓት ሆነዋል እንላለን?

4. የደቂቃ ቆጣሪ ጨረር ከ12 ሰዓት ተነስቶ 1 ላይ ስደርስ ስንት ደቂቃ አለፈ እንላለን?

5. የሰዓት ቆጣሪ ጨረር ከ12 ሰዓት ተነስቶ 1 ላይ ቢደርስ የደቂቃ ቆጣሪ ስንት ደቂቃ ሄደ?

# 11.2 ሰዓት እና ደቂቃ

## ትግበራ 11.2

መገርቱ የግድግዳ ሰዓትን ካያች በኃላ 10 : 40 መሆኑን ተናገረች፡፡ ገልገሉ ደግሞ ለአስራ አንድ ሰዓት ሃያ ጉዳይ አለ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ልጆች ሰዓቱን ያነበቡበት ሁኔታ ልዩነት አለውን? ተወያዩበት፡፡

**አስተውል/ይ**

የሰዓት እና የደቂቃ ተዛምዶ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

ሰዓትን ወደ ደቂቃ ለመቀየር የተሰጠውን ሰዓት በ60 እናባዛለን፡፡

ደቂቃን ወደ ሰዓት ለመቀየር የተሰጠውን ደቂቃ ለ60 ማካፈል ነው፡፡

### ምሳሌ 3

2 ሰዓት = ________ደቂቃ ይሆናል፡፡

**መፍትሄ**

2 × 60 = 120 ደቂቃ

ስለዚህ 2 ሰዓት 120 ደቂቃ

### ምሳሌ 4

180 ደቂቃ =______ ሰዓት ይሆናል፡፡

**መፍትሄ**

180 ደቂቃ = 60 ደቂቃ+ 60 ደቂቃ+ 60 ደቂቃ

= 1 ሰዓት + 1 ሰዓት + 1 ሰዓት

= 3 ሰዓት ይሆናል፡፡ . ወይንም 180/60 = 3

## መልመጃ 11.2

1. ከዚህ በታች የተሰጠውን ሠንጠረዥ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የቀረውን ሙሉ/ይ፡፡

| ሰዓት | 1 | 2 | | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ደቂቃ | 60 | | 150 | | |

2. ከዚህ በታች የተሰጡትን ሰኣት በቁጥር ፃፍ/ፊ፡፡

ሀ. ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ

ለ. ለሁለት ሰዓት አምስት ጉዳይ

ሐ. አስር ሰዓት ከሃያ

መ. ለአንድ ሰዓት ሃያ አምስት ጉዳይ

3. የጠዋቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ 4 ሰዓት ይወስዳል። የከሰዓት በኃላ ደግሞ 2 ሰዓት ይወስዳል። በአጠቃላይ በቀን ውስጥ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚወስደው ምን ያህል ሰዓት ነው?
4. ሙለታ የሂሳብ ትምህርት የቤት ስራ ለመስራት 25 ደቂቃ ይወስድበታል። እንዲሁም ደግሞ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የቤት ስራ ለመስራት 15 ደቂቃ ብወስድበት በአጠቃላይ የቤት ስራውን ሰርቶ ለመጨረስ ስንት ደቂቃ ይወስድበታል?
5. ገለታ የሂሳብ ፈተና ሰርቶ ለመጨረስ 38 ደቂቃ ወሰደበት። ሮቤራ ደግሞ 45 ደቂቃ ብወስድበት ገለታ በስንት ደቂቃ ከሮቤራ ቀድሞ ጨረሰ ?

## 11.3 ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት እና አመታት

### የጊዜ አቆጣጠር ዩኒቶች ተዛምዶ

**ትግበራ 11.3**

ጉቱ ዛሬ የአንደኛ አመት የልደት ቀኑን ያከብራል።

ሀ. ጉቱ ከተወለደ ስንት ወሩ ነው?

ለ. ጉቱ ከተወለደ ስንት ሳምንታት ሆኖታል?

በጊዜ ዩኒቶች መካከል ያለው ተዛምዶ እንደሚከተለው ተገልጿል።

| | |
|---|---|
| 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ | 1 ወር = 30 ቀናት |
| 1 ቀን = 24 ሰዓት | 1 ዓመት = 52 ሳምንታት |
| 1 ሳምንት= 7 ቀናት | 1 ዓመት = 12 ወራት |

**ምሳሌ 5**

2 ቀናት ስንት ሰዓት አለው?

**መፍትሄ**

1 ቀን 24 ሰዓት አለው።

ይኸውም $2 \times 24 = 48$ ይሆናል።

ስለዚህ 2 ቀናት 48 ሰዓት አለው።

**ምሳሌ 6**

7 ቀናት ስንት ሰዓት አለው?

**መፍትሄ**

1 ቀን 24 ሰዓት አለው።

ይኸውም $7 \times 24 = 168$ ይሆናል።

ስለዚህ 7 ቀናት 168 ሰዓት አለው።

**ምሳሌ 7**

6 ወራት ስንት ሳምንታት አለው?

**መፍትሄ**

1 ወር 4 ሳምንታት አለው።

ይሄውም $4 \times 6 = 24$ ይሆናል።

ስለዚህ 6 ወራት 24 ሳምንታት አለው።

**መልመጃ 11. 3**

1. ጂቱ እና ጓደኞቿ ለ1 ሰዓት ሲጨወቱ ነበር። ለስንት ደቂቃ ተጫዋቱ?
2. ደራርቱ ለሁለት ሳምንታት አያቷ ጋር ለማሳለፍ ወደ ሞጆ ከተማ ተጓዘች። ደራርቱ ለስንት ቀናት ሞጆ ከተማ ቆየች?
3. በአንድ አመት ውስጥ የትምህርት ቀናት 10 ወራት ናቸው። በአንድ አመት ውስጥ የትምህርት ቀናት ስንት ሳምንታት ይሆናል?
4. ሁለት አመት ስንት ወራት አለው?
5. 36 ወራት ስንት አመት አለው?
6. 156 ሳምንታት ስንት አመታት አለው?

## 11.4 የኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር

### ትግበራ 11.4

1. የኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ስንት ወራት አለው?
2. የኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ከየትኛው ወር ይጀምራል?
3. የኢትዮጵያ ወራትን ከመጀመሪያ ወር በመነሳት በቅደም ተከተል ሁሉንም ዘርዝረህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

**ማስታወሻ**
የኢትዮጵያ ቀናት አቆጣጠር 13 ወራት አለው፡፡ አስራ ሁለቱ ወራት እንዳንዳቸው 30 ቀናት ሲኖራቸው 13 ኛው ወር ግን 5 ቀናት ያለውና በየ4 አመቱ 6 ቀናት ይኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቀናት አቆጣጠር የምጀምረው ከመስከረም ነው፡፡

**መልመጃ 11.4**

ከዚህ በታች የተሰጠውን የቀን አቆጣጠር በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

| ሰኔ 2003 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

1. በተሰጠው የቀን አቆጣጠር ላይ የወሩ መጀመሪያ በየትኛው ቀን ላይ ይውላል?
2. በተሰጠው የቀን አቆጣጠር ላይ የወሩ መጨረሻ በየትኛው ቀን ላይ ይውላል?
3. በተሰጠው የቀን አቆጣጠር ላይ የወሩ የመጀመሪያ እሁድ ቀኑ ስንት ነው?
4. ከሰኔ 2003 ቀጥሎ የሚመጣዉ ወር ሐምሌ 2003 ነው፡፡ ከላይ በተሰጠው የቀን አቆጣጠር ላይ ሐምሌ 2003 የትኛው ቀን ይጀምራል?

## 11.5 ከኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ጋር ተዛምዶ ያላቸው የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**ምሳሌ 8**

ገላና ከጎባ ተንስቶ በእግር ተጉዞ 9 ሰዓት ላይ ሮቤ ደረሰ፡፡ የመንገዱ ርቀት 2 ሰዓት የምወስድበት ከሆነ ገላና ስንት ሰዓት ላይ ከጎባ ተነሳ?

**መፍትሄ**

**የተሰጠው** : የመድረሻ ሰዓት = 9:00 የወሰደት ሰዓት = 2 ሰዓት

**የሚፈለገው** : የመነሻ ሰዓት?

**ስሌት**: የመነሻ ሰዓት = የመድረሻ ሰዓት — የወሰደት ሰዓት

= 9: 00 - 2: 00 = 7: 00

ስለዚህ ገላና ከንባ የተነሳበት ሰዓት 7:00 ነዉ፡፡

## መልመጃ 11.5

1. ጃላኔ 12:30 እራት ማዘጋጀት ጀመረች፡፡ አዘጋጅታ ለማጠናቀቅ 1:30 ቢፈጅባት በስንት ሰዓት ላይ አዘጋጅታ ትጨርሳለች?
2. ቶለሼ ጠዋት 1:40 ላይ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ተገኘች፡፡ ትምህርት የሚጀምረው 2:30 ነው፡፡ ቶለሽ ስንት ደቂቃ ቀድማ ተገኘች?
3. ጀቤሳ 11:00 ሰዓት ላይ ባቡር ጣቢያ ደረሰ፡፡ ለመድረስ 1 ሰዓት ቢፈጅበት በስንት ሰዓት ወደ ባቡር ጣቢያ መጓዝ ጀመረ?
4. ለሜሳ የአያቱ ቤት ለመሄድ በ3:30 ተነስቶ 3 ሰዓት ወሰደበት፡፡ በስንት ሰዓት ላይ ደረሰ?
5. ከዚህ በታች የተሰጠውን ቀላል የኢትዮጵያ የቀናት አቆጣጠር ላይ በመመርኮዝ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

| **ሐምሌ 2013** | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

ሀ. የጋዲሴ የልደት ቀን ሐምሌ 17 ከሆነ በምን ዕለት ተወለደች?

ለ. ሐምሌ 30 በምን ዕለት ላይ ይውላል?

ሐ. ከዚህ በላይ እንደተሰጠው የቀን አቆጣጠር ሐምሌ 30 በምን ዕለት ይውላል?

መ. የትምህርት ቤት የድራማ ቡድን ሁል ጊዜ በየሳምንቱ ሀሙስ ሀሙስ ይሰበሰባሉ፡፡ በዚህ በሐምሌ ወር ውስጥ ስንት ጊዜ መሰብሰብ ይችላሉ?

ሠ. ረቡዕ ነሐሴ የመጀመሪያው ሳምንት ቀኑ ስንት ነው?

ረ. ሦስተኛው ሀሙስ በምን ቀን ላይ ይውላል?

ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

# ሒሳብ

## የመምህራን መምሪያ

## 3ኛ ክፍል

ዋጋ ________________